ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ
Wisdom at the Source of the Blue Nile

# ናይል
# THE NILE





ኢ-ሜይል፡- bduinfo63@gmail.com or gracetsegi@gmail.com ድረ-ገጽ፡- http://www.bdu.edu.et የፌስቡክ ገጽ፡- www.facebook.com/bduethiopia

2ኛ ዓመት፣ ቁጥር 11፣ ታህሳስ 2007


## የሱዳን የሙዚቃ ቡድን በዩኒቨርሲቲው ዝግጅቱን አቀረበ

## Who was the seed?

Melaku Wale (PhD)

## የራያ ቆቦ የባሕል የሙዚቃ ቡድን ዝግጅቱን አቀረበ

## እንግዳ

በሂሩት አድማሱ

## ማህበረሰብ ተኮር ምርምር በሬዕይ ጥበብ 2017

በባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)



Sudanese cultural team performing modern and traditional Sudanese songs to BDUs' community



Tourism week celebrated at BDU

እውነትን መፈለግና ለሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!

ናይል
THE NILE

በኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
የውስጥ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ክፍል
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

የአማካሪ ቦርድ አባላት
አቶ ሞገስ አብርሃ
ዶ/ር ጌታቸው ፍስሃ
ዶ/ር ጥጋብ በዜ
ዶ/ር እንየው ታደሰ
አቶ በላይነህ ወርቁ
ወ/ሪት እንዳስ ቃሶ
አቶ ፈታሒ በቃሉ
አቶ ብሩክ ከተማ
አቶ ቴዎድሮስ ካሳዬ

ዋና አዘጋጅ:-
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

ም/ዋና አዘጋጆች
ሀሰን ዑስማን
ሂሩት አድማሱ

አርታኢዎች
ይናገር ተ/ስላሴ
አብነት ሰለሞን
ነብዩ ንጉሴ

ዘጋቢዎች:-
አምሳሉ ጥላሁን
የማነ ገብሩ
ታድዬ አስማረ
ትግስት ዳዊት
አበባ ሐብቱ
ሙሉጎጃም አንዷለም

አምደኞች:-
ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
መላኩ ዋለ (ዶ/ር)
ሂሩት አድማሱ
ታምሩ ደለለኝ
አረጋዊ ሰለሞን
መክሊት ጋረደው

ግራፊክስና ሌይአውት:-
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

ፎቶ አንሺዎች:-
ታምራት አታላይ
ሙሉጌታ ዘለቀ

የኮምፒውተር ጽሁፍ:-
ፋንታነሽ ላቀው
ታሪክ ታደሰ
የሻለም መንግስቴ

ትራንስፖርት:-
ማናለ ኃይሌ

መልእክተኞች:-
ቃልኪዳን አወቀ
ንብረት ታፈረ

ስልክ:- +251 583206088

# አበይት ዜናዎች

## ለጤና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጠ

አበባ ሐብቱ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዳይሬክቶሬት ከዲኬት ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር በዩኒቨርሲቲው ክሊኒኮች ለሚሰሩ የጤና ባለሙያዎች አቅም የሚያጎለብት ደረጃውን የጠበቀ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስችል የሁለት ቀን ስልጠና ሰጠ፡፡

የዩኒቨርሲቲው ኤች አይ.ቪ. ኤድስ መከ/መቆ/ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ሲ/ር ማርታ አስማረ የስልጠናውን አላማ ሲገልጹ ተማሪዎች የስነ-ተዋልዶ ችግር ሲያጋጥማቸው በግቢ ውስጥ ካሉ ክሊኒኮች ይልቅ ከግቢ ውጭ አገልግሎት ሲፈልጉ እንደሚታዩና አገልግሎቱን በተመለከተ ብዙ ጊዜ የሚነሱ የተማሪዎችን ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ ለባለሞያዎች ስልጠና በመስጠት ተማሪዎች ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን በመቆጠብ እንዲሁም ከትምህርታቸው ሳይስተጓጎሉ መታደግ እንዲቻል ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ ሲ/ር ማርታ አክለውም የጤና ባለሞያዎች በስልጠናው በቂ ግንዛቤ አግኝተው ተማሪዎች የነገ አገር ተረካቢ መሆናቸውን በማመን በትጋትና በታማኝነት አገልግሎት እንዲሰጧቸው ነው፡፡ ስልጠናው በዋናው ግቢ የተዋልዶ-ጤና ማዕከል የተሰጠ ሲሆን የስልጠናው ተሳታፊዎች ስልጠናው አስፈላጊ እንደሆነና በቂ ግንዛቤ እንዳገኙበት ገልፀው በቀጣይ በእውቀት ላይ የተመሰረተ አገልግሎት እንደሚሰጡ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል፡፡

## የአካል ጉዳተኞች ቀን ተከበረ

የማነ ገብሩና ታድዬ አስማረ

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ 23ኛው ዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች ቀን ‹‹አካል ጉዳተኞች የቴክኖሎጅ ተጠቃሚ ለማድረግ ዘላቂ ልማት እናረጋግጥ›› በሚል መሪ ቃል በልዩ ልዩ ዝግጅቶች ተከበረ፡፡

ቀኑ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የትምህርትና ሥነ-ባህሪ ፋኩልቲ ሲከበር የዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ማተቤ ተፈራ አካል ጉዳተኞች የሚፈለጉትን ተግባር ለማከናወንና የልማት አጋዥ ሀይል እንዲሆኑ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የስርዓተ ፆታ ጽ/ቤት ባዘጋጀው በአል ላይ የተገኙት የፕሬዝዳንት ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ምህረቴ ዋለ አካል ጉዳተኞች በሁሉም ዘርፍ ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ተስማሚ የቴክኖሎጅ ውጤት ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው ዩኒቨርሲቲው የአካል ጉዳተኞችን የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ እንደሆን ገልጸዋል፡፡

ጽ/ቤቱ ባዘጋጀው በአል ላይ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የህግ ትምህርት ቤት መምህር ረዳት ፕሮፌሰር አቶ በላይነህ አድማሱ ‹‹The right of persons with disabilities to access Technology to ensure sustainable development›› በሚል ርዕስ ጥናታዊ ፅሁፍ አቅርበዋል፡፡ ቀደም ሲል አካል ጉዳተኛ በደረሰበት የአካል ጉዳት ውስንነት ምክንያት መስራት የማይችል፣ የበጎ አድራጎት ተመፅዋችና በማንኛውም የልማት እንቅስቃሴ ላይ ተሳትፎ እንደሌለው ተደርጎ ትርጉም ሲሰጠው እንደነበር ለዚህም ዋና መንስኤ በማህበረሰቡ ውስጥ የነበረው የአመለካከት ውስንነት መሆኑን አቶ በላይነህ በጥናታዊ ፅሁፋቸው ገልጸዋል፡፡ በአሁን ጊዜ የአካል ጉዳተኞችን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ተሳትፎ ለማጐልበት ደንቦችና ድንጋጌዎች ተግባራዊ በመደረጋቸው ምቹ ሁኔታዎች እየተፈጠረላቸው መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የአካል ጉዳተኞች ቀን በትምህርትና ሥነ-ባህሪ ፋኩልቲ ሲከበር የፋካልቲው ዲን አቶ አስራት ደርብ አካል ጉዳተኝነት በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰት በመሆኑ ማህበረሰቡ በአካል ጉዳተኝነት ላይ ያለውን የተሳሳተ አመለካከት በመቀየር አካል ጉዳተኞች መስራት እንደሚችሉ ተገንዝቦ ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

ፋኩልቲው አካል ጉዳተኞች ላይ ትኩረት በመስጠት የልዩ ፍላጐት ት/ክፍል በመክፈት ባለሙያዎችን በማሰልጠንና ስልጠናዎችን በማዘጋጀት የግንዛቤ ስራ እየሰራ ይገኛል፡፡ በክረምት ወራት 29 ለሚደርሱ አይነ-ስውራን ተማሪዎች የኮምፒውተር ስልጠና በመስጠት የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ በማድረግ በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ያሉ ችግሮችን በተወሰነ ደረጃ እንዲቀረፍ አድርጓል፡፡

አካል ጉዳተኞች የእለት እለት ተግባራቸውን በተቀላጠፈና በቀላል መንገድ ለመከወን የሚያስችላቸው ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለማድረግ የዘንድሮው የአካል ጉዳተኛ ቀን መሪ ቃል አካል ጉዳተኞችን የቴክኖሎጅ ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑ ታውቋል፡፡

## የሱዳን የሙዚቃ ቡድን ዝግጅቱን አቀረበ

ታድዬ አስማረ

የሱዳን የባህልና የዘመናዊ ሙዚቃ የልኡካን ቡድን በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ስፖርት አካዳሚ ስታዲየም በመገኘት ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የተለያዩ ጣዕመ ዜማዎችን አቅርቧል፡፡ ቡድኑ ሱዳንን ሊያስተዋውቁ የሚችሉ ጣዕመ ዜማዎች በማቅረብ የዩኒቨርሲቲውን ማህበረሰብ አዝናንቷል፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ ለልኡካን ቡድኑ አቀባበል ባደረጉበት ወቅት ኢትዮጵያና ሱዳን የረዥም ጊዜ ታሪካዊ ግንኙነት እንዳላቸው አውስተው በጋራ ጥቅምና ፍላጐት ላይ የተመሰረተው ግንኙነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ በመምጣቱ በተለይ በሰላምና ደህንነት፣ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚና ፖለቲካ ጉዳዮች ላይ አብረው እየሰሩ እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡ የሙዚቃ ዝግጅቱ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት እንደሚያጠናክረው አመልክተዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲው በሱዳን ከሚገኙ ካርቱም እና ኒያላ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የተማሪዎች ልውውጥ እንዲሁም ምሁራኑ በዓባይ ተፋሰስ ዙሪያ በጋራና በተናጠል ምርምር በማድረግ የተፋሰሱ ሀገራት ህዝቦችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ሥራ መስራት የሚያስችላቸውን ግንኙነት መፍጠር መቻሉን ገልጸዋል፡፡

የሱዳኑ ፕሬዚዳንት ኦማር ሀሰን አልበሽር ዩኒቨርሲቲው በ2006 ዓ.ም በዓባይ ዙሪያ ባዘጋጀው ዓለም አቀፍ አውደ ጥናት ላይ መገኘታቸው የሚታወስ ሲሆን በየዓመቱ ሚያዚያ 20 የሱዳን ቀን ተብሎ እንዲከበር ዩኒቨርሲቲው ቃል በገባው መሰረት በዚህ ቀን የሱዳን ምሁራን በዩኒቨርሲቲው ተገኝተው ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እውቀታቸውን እንዲያካፉሉ መድረክ እንደሚዘጋጅ ታውቋል፡፡

የሙዚቃ ቡድኑ በቤኒሻንጉል ክልል አሶሳ ከተማ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተከበረውን 9ኛው የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በዓል ለማድመቅ ወደ ኢትዮጵያ መምጣቱ ይታወሳል፡፡

To follow the latest news about BDU, check out our website:- **http://www.bdu.edu.et** or facebook address:- **www.facebook.com/bduethiopia**

ዜናዎቻችንን በድረ-ገጻችን http://www.bdu.edu.et እና በፌስቡክ ገጻችን www.facebook.com/bduethiopia መከታተል ይችላሉ፡፡

# መልዕክቶችና አስተያየቶች

## ርዕሰ-አንቀጽ

### አፍሪካዊ ግንኙነቶችን አጠናክረን እንቀጥላለን!

9ኛው የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን ህዳር 29 ቀን 2007 ዓ.ም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ርዕሰ መዲና አሶሳ ላይ በድምቀት ሲከበር የሱዳን ባህላዊና ዘመናዊ የሙዚቃ የልኡካን ቡድን በበአሉ ላይ በመገኘት ለበአሉ ድምቀት የራሱን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ የልዑካን ቡድኑ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ስፖርት አካዳሚ ስታዲዮም በመገኘትም ለዩኒቨርሲቲው ማሕበረሰብ የተለያዩ ጣዕመ ዜማዎችን አቅርቧል፡፡ ዝግጅቱን በተሳካ ሁኔታ እንዲያቀርብ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ መድረኮችን በማዘጋጀትና የደመቀ አቀባበል በማድረግ የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ይህ ዝግጅት በሱዳንና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን የረጅም ጊዜ ታሪካዊ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን የበለጠ ለማጠናከር ሚናው ከፍ ያለ ነው፡፡

በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል ያለው ግንኙነት ድንበርና የተፈጥሮ ሀብት ከመጋራት ባለፈ ጠንካራ የሕዝብ ለሕዝብ ትስስር ያለው ነው፡፡ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን ግንኙነት በይበልጥ በማጠናከር በሱዳን ከሚገኙት ካርቱም እና ኒያላ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ስምምነት በመፍጠር የተማሪዎች ልውውጥና ምሁራን በዓባይ ዙሪያ በጋራና በተናጠል ምርምር በማድረግ በተፋሰሱ ሀገራት የሚገኙ ሕዝቦችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ስራ እየሠራ ይገኛል፡፡ ይህም ዩኒቨርሲቲው ከአፍሪካ ሀገራት ጋር ያለውን ወዳጅነት እያጠናከረ ስለመሆኑ አንድ ማሳያ ነው፡፡

ኢትዮጵያ የቀድሞውን የአፍሪካ ህብረት መመስረትን ጨምሮ ለአህጉሪቱ የነፃነት ተምሳሌት በመሆን ለብዙ የአፍሪካ ሀገራት አርአያ በመሆን ቆይታለች፡፡ በአህጉሪቱ ውስጥ በተለይ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ በሚከሰቱ ግጭቶች መፍትሄ ለማምጣት በሚደረገው ጥረት ላይ ተሳትፎዋ በጣም የጎላ ነው፡፡ በዚህ አኳያ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ምርምር በማድረግና የመፍትሄ ሃሳቦችን በማመንጨት ትልቅ ድርሻ አላቸው፡፡ ኢትዮጵያ በአህጉሪቱ ያላትን ተሣትፎ ለመቀጠል የትምህርት ተቋማቱ የድርሻቸውን መወጣት እንዳለባቸው ይታመናል፡፡

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲም ከሱዳን ጋር ብቻ ሳይሆን ከሌሎች የአፍሪካ አገራት ጋር ግንኙነት በመፍጠር በአህጉሪቱ እድገትና ብልጽግና ላይ ያለውን ተሣትፎ በማሳደግ ከአፍሪካ ከሚገኙ አስር ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ለመሆን ራዕይ ሠንቆ እየተጋ ይገኛል፡፡

ዩኒቨርሲቲው አለም አቀፍ የስብሰባ ከተማ (ኮንፈረንስ ሲቲ) በሆነችውና አለም አቀፋዊና አህጉራዊ ጉባኤዎች በሚዘጋጁባት ባሕር ዳር ከተማ እንደመገኘቱ ሀገራዊም ሆነ አህጉራዊ ችግሮችን ለመፍታት በመማር ማስተማር ዘርፍ በዕውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት ብቁ የሆኑ ዜጎችን በማፍራት እንዲሁም በምርምር ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሌሎች ዘርፎች ላይ የሚታዩ ችግሮችን ፈትሾ በመለየትን፣ የመፍትሄ ሀሳቦችን በማመንጨት እንዲሁም አዳዲስ የሀብት ምንጮች እንዲፈጠሩና እንዲስፋፉ አስተዋጽኦ ለማድረግ እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ ይህን ሀገራዊ ሀላፊነት ተግባራዊ ለማድረግ የዩኒቨርሲቲው አመራሮች፣ መምህራን፣ ተማሪዎችና የአስተዳደር ሰራተኞች የበኩላቸውን ሃላፊነት መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲው በእውቀት፣ በቴክኖሎጂ፣ በሳይንስና በሀብት ፈጠራ ለአፍሪካ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማበርከት እንዲሁም ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ጋር ወዳጅነቱን የበለጠ በማጠናከር ለመስራት ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል፡፡ ጥረቶቹን ውጤታማ ለማድረግ ዩኒቨርሲቲው ያለበትን ጠንካራ ጎኖች ይበልጥ በማጠናከርና ክፍተቶችን በመሙላት የሀገሪቱንና የአህጉሪቱን እድገት ለማፋጠን፣ ችግሮችን ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ በመፍታት፣ በቴክኖሎጂና ሳይንስ ላይ ትኩረት በመስጠት፣ ብቁ ባለሙያዎችን በማፍራት የበኩሉን አስተዋጽኦ ማበርከቱን አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

**እውነትን መፈለግና ለሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!**

## ቁልፍ መልዕክት

### ማህበረሰብ ተኮር ምርምር በራዕይ ጥበብ 2017

ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት

የማህበረሰብ ተኮር ምርምር በበርካታ መንግስዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ተደጋግሞ ይነሳል፡፡ ለመሆኑ በእኛ ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ ማህበረሰብ ተኮር ምርምር ሲባል ምን ማለት ነው ብለን ራሳችንን በመጠየቅ የተለያዩ ሀሳቦችን የምናንሸራሽር የዩኒቨርሲቲያችን ማህበረሰቦች ብዙ እንደምንሆን መገመት ይቻላል፡፡ በተለያዩ ሀገራት ያሉ ምሁራን ሀሳቡን በተለያዩ አግባቦች ይገልፁታል፡፡ በዚህ አጭር ጽሑፍ የሀሳቡን ምንነት ዋቢ ጽሑፎችን በመጥቀስ ለመተንተን አንሞክርም፡፡ የጽሑፉ አላማ ማህበረሰብ ተኮር ምርምር በራዕይ ጥበብ 2017 የተቀመጠበትን አግባብ በመግለጽ በቀጣይ ውይይትና ክርክር የምንከተለው መስመር ላይ ያለንን ግንዛቤ የሚያሳድግ ነው፡፡

በራዕይ ጥበብ 2017 ማህበረሰብ የምንላቸው የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦችን ነው፡፡ የማህበረሰብ ተኮር ምርምር ሲባል ደግሞ የእነሱን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዕድገትና ብልጽግና የሚያመጣውን ውጤት በመመርመር ማግኘትና ተግባራዊ የሚሆንበትን አሰራር ማመላከትን እንዲሁም ሰርቶ ማሳየትን ያካተተ ሀሳብ ነው፡፡ ይህን መሰረታዊና ጥቅል ሀሳብ በየዘርፉ ምሳሌ በመውሰድ የበለጠ የምንገነዘብበትን ሁኔታ መፍጠር ይቻላል፡፡

ማህበረሰብ ተኮር ምርምርን ከሀገራችን ማህበራዊ ዘርፍ ዕድገት አኳያ ለማየት የትምህርቱንና የጤናውን ዘርፍ በመውሰድ ማቅረብ ይቻላል፡፡ በትምህርት ላይ ማህበረሰብ ተኮር ምርምር ስንል ለማህበረሰባችን በጐልማሶች፣ በአንደኛ ደረጃ፣ በሁለተኛ ደረጃ፣ በኮሌጅና ዩኒቨርሲቲ የሚሰጡ ትምህርቶች የሚፈለገውን ዕውቀት፣ ክህሎትና አጠቃላይ አመለካከት ከማስጨበጥ አንፃር በሚገባ በመፈተሽና ጉድለት ካለ የጉድለቱን ምክንያት በሚገባ በመለየት መፍትሄ ማስቀመጥን ያካትታል፡፡ በዚህ የምርምር ዘርፍ ውስጥ ተዝቆ የማያልቅ ምርምር ማካሄድና ቀጣይነት ባለው መልኩ ማህበረሰቡን ሊጠቅሙ የሚችሉ ሀሳቦች ማግኘት ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በጤና ዘርፍ ላይ የማህበረሰባችንን ጤና ለመጠበቅና ከታመሙ ለማዳን የሚያስችሉ አሰራሮችን የተለያዩ የአካባቢ ሁኔታዎችን ባገናዘበ መልኩ መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን የመቀመርና በተግባር የሚውሉበትንም መንገድ በሰርቶ ማሳያ መርህ ማመላከትን ያቅፋል፡፡

የማህበረሰብ ተኮር ምርምር ከኢኮኖሚያዊ ዘርፍ አንፃር ስናየው አሁን ለሀገራችን ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት የሆኑትን ዘርፎች በሚገባ ፈትሾ የበለጠ ውጤታማ የሚሆኑበትን ዘዴ መቀየርንና አዳዲስ የሀብት ምንጮች በሀገራችን እንዲፈጠሩና እንዲስፋፉ ምቹ ሁኔታዎችን በተግባር ማሳየትን ያካትታል፡፡ በዚህ ዘርፍ በርካታ እምርታ ሊመዘገብባቸው የሚችሉ ሁኔታዎች አሉ፡፡ እዚህ ላይ የገጠሩን ህዝባችንን ብንወስድ የአስተራረስ ዘዴውን፣ የሰብልና የመሬት አጠቃቀሙን፣ ሰብል የሚሰበስብበትን አግባብ፣ ከተሰበሰበ በኂላ የሚቀመጥበትንና ለተጠቃሚው እስኪደርስ ድረስ ያለው ሂደት በሚገባ በመፈተሽና ተገቢውን ዘመናዊ አሰራር በመዘርጋት ልናገኝ የምንችለው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ እነዚህ ዘርፈ ብዙ ስራዎች በርካታ የምርምር ስራዎችን የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ የእንጀራን አሠራር በሚገባ ፈትሾ ማገዶ በሚቆጥብና ጉልበትን በማይጨርስ መልኩ እንዲሠራ ብናደርገው የምናተርፈው ደንና የሰው ጉልበት በጣም ብዙ ነው፡፡ ሌሎች ሀገሮች እየበለፀጉበትና ዋነኛ የሀብት ምንጫቸው እየሆነ የመጣውን የኢንፎርሜሽንና ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ ላይም በርካታ የስራ ዕድሎችን እና ሀብቶችን መፍጠር ይቻላል፡፡

ማህበረሰብ ተኮር ምርምር ለፖለቲካዊ ዕድገትም የሚያበረክተው ፋይዳ ትልቅ ነው፡፡ በአለማችን ላይ የተሞከሩትንና አሁንም እየተተገበሩ ያሉትን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚዎች በሚገባ በመፈተሽና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ጠንካራና ደካማ ጐናቸውን በማሳየት ማቅረብ በራሱ የማህበረሰባችንን ፖለቲካዊ ግንዛቤ ስለሚያሳድግ ጠቀሜታው ትልቅ ነው፡፡ ተያያዥነት ባለው መልኩ በሀገራችን ታሪክ ስንከተላቸው የነበሩትን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚዎች በሚገባ በማጥናትና ያስገኙትንም ውጤት በማሳየት ከታሪካችን የምንማርበትን ሁኔታ በመፍጠር ምርምር የሚጠይቅና ለሀገራችንም ያለው ጥቅም ዘርፈ ብዙ ከመሆኑ ባሻገር በሀገራችን ታሪክ ላይ መግባባት ለመፍጠር ያግዛል፡፡ በቀጣይነትም አሁን ያለንበትን ተጨባጭ ሁኔታ (አገራዊ፣ አህጉራዊና አለማቀፋዊ) በሚገባ በመፈተሽና ጥልቅ ትንተና በማድረግ አሁን እየተከተልነው ያለውን ልማታዊ ዲሞክራሲያዊ ፖለቲካ ኢኮኖሚ የበለጠ እንድንረዳውና በሂደትም እያዳበርነው እንድንሄድ ዕድል የሚፈጥሩ ውጤቶችን ማግኘት ያስችለናል፡፡

ማህበረሰብ ተኮር ምርምር በራዕይ ጥበብ 2017 በወፍ በረር ዕይታ ሲቀመጥ ይህን ይመስላል፡፡ እነዚህን በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃለው የቀረቡ ሀሳቦችን መሰረት አድርገን በሂደት በምናደርገው ውይይትና የተግባር ስምሪት ሀሳቡን እያጠናከርን እንሄዳለን፡፡

ራዕይ ጥበብ 2017ን እናሳካለን!!!

# አበይት ዜናዎች...

## የምክር ቤት አባላት በዩኒቨርሲቲው ጉብኝት አደረጉ

አምሳሉ ጥላሁን

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሰው ሃብት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በመማር ማስተማር፣ በምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎት እያከናወነ ያለውን ስራ ጎበኙ፡፡

የኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ አቶ ኢያሱ ወርቅነህ ዩኒቨርሲቲው በመማር ማስተማር፣ በምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፍ ትኩረት በመስጠት እየሰራ መሆኑን መረዳታቸውን ገልጸው አዳዲስ የማስፋፊያ ግንባታዎች በማካሄድ ለማህበረሰቡ የስራ እድል መፍጠር መቻሉን አድንቀዋል፡፡ በተለይ የዩኒቨርሲቲው የቴክኖሎጂ ግቢና የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ተቋም የስራ አፈፃፀማቸው የተሻለ መሆኑን ምክትል ሰብሳቢው ገልፀዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲ ያከናወናቸው በርካታ ውጤታማ ስራዎች እንዳሉ ሁሉ አንዳንድ የታዩ ውስንነቶች እንዲሻሻሉም ቋሚ ኮሚቴው ማሳሰቢያ ሰጥቷል፡፡

ቋሚ ኮሚቴው ዩኒቨርሲቲው ሴቶችን ወደ አመራርነት ለማምጣት፣ በሴት ተማሪዎች ላይ የሚደረገውን ፆታዊ ትንኮሳ ለመከላከል፣ የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪዎችን በምርምሩ ዘርፍ ያላቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ፣ በስነ ተዋልዶ ዙሪያ ዩኒቨርሲቲው ምርምር በማድረግና በዩኒቨርሲቲው አካባቢ ተማሪዎችን ለአጉል ሱስ የሚዳርጉ የንግድ እንቅስቃሴዎች ለማስወገድ ምን እየሰራ እንደሚገኝ ጠይቋል፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ በቋሚ ኮሚቴው የተሰጡት አስተያየቶችና ጥያቄዎች ገንቢና ለወደፊት ስራ ግብአት እንደሚሆኑ ገልጸው ዩኒቨርሲቲው ሀገራችን ኢትዮጵያ በ2017 ዓ.ም መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለመሰለፍ ያላትን ግብ ለማሳካት ዩኒቨርሲቲ የራሱን አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡ ለዚህም ዩኒቨርሲቲውን የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለማድረግ ከ15 በላይ የPhD ፕሮግራሞችን ለመክፈት ፤ የትምህርት ጥራትን ለማምጣት ቤተ-ሙከራዎችን በማሟላትና የመምህራንን እና የአመራሮችን አቅም በመገንባት እንዲሁም የሚያካሂደውን የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት ከሀገሪቱ ዓላማ ጋር በማስተሳሰር እየሰራ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የዩኒቨርሲቲው መሪ አስተሳሰብ ቴክኖሎጂን ወደ ሃብት በመቀየር በመምህራንና በተማሪዎች የሚፈጠሩ ቴክኖሎጂዎችን ወደ ሃብት መቀየርና የሙያው ባለቤቶችን በሃገር ደረጃ ለማስተዋወቅ እየሰራ እንደሆነ ፕሬዝዳንቱ ተናግረዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲው የምርምር ማዕከላትን በማቋቋም በትምህርት፣ በውሃ፣ በጤና ላይ ትርጉም ያለው ስራ እየሰራ እንደሚገኝ፤ የራዕይ 2017ን መንገድ ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ለማሳየት የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ሲሰራ እንደቆየና ወደፊትም አጠንክሮ እንደሚሰራና ከቋሚ ኮሚቴ የተጠቀሱትን ጠንካራ ጎኖች የበለጠ አጠንክሮ እንደሚሰራ እንዲሁም ክፍተቶችን በማስወገድ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብና አመራሩ በጋራ ሊሰሩ እንደሚገባ የዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አመራሮች ተናግረዋል፡፡

በጉብኝቱ ወቅት በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የሚገኙ ግቢዎች፣ በምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት እየተሰሩ ያሉ ስራዎች፣ የማሪታይምና የስፖርት አካዳሚዎች፣ በመገንባት ላይ የሚገኘውን የመምህራን የጋራ መኖሪያ ቤቶች፣ አዳዲስ የማስፋፊያ ግንባታዎች፣ ቤተ- ሙከራ ቤቶች፣ ሰርቶ ማሳያዎች፣ ቤተ-መጽሐፍት፣ የአካል ጉዳተኛ ማደሪያ ክፍሎች፣ የመማሪያና የማደሪያ ክፍሎች እንዲሁም የተማሪዎች ምግብ ቤትን ጎበኝተዋል፡፡

## ኩነቶች ለቱሪዝም ዕድገት ያላቸው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑ ተገለጸ

ሙሉጎጃም አንዱአለም

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ «The role of Events for promoting Tourism Destinations» በሚል መሪ ቃል በዩኒቨርሲቲው ስፖርት አካዳሚ ስታዲየም የቱሪዝም ሣምንት ተከበረ፡፡

በበአሉ ላይ የተገኙት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ተ/ምክትል ፕሬዚደንት አቶ ሞገስ አብርሃ የቱሪዝምና ሆቴል ማኔጅመንት ትምህርት በቅርብ ጊዜ ከተከፈቱት የትምህርት ክፍሎች አንዱ እንደሆነ ገልጸው የበአሉ መከበር ተማሪዎች ተግባር ተኮር እውቀት እንዲያገኙ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለውና እንደዚህ አይነት ዝግጅቶች የበለጠ ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ጠቁመዋል፡፡ አቶ ሞገስ አውደ ርዕዩ እንዲሳካ ጉልህ አስተዋጽኦ ያደረጉትን የአማራ ክልል ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ፣ የባሕር ዳር ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም መምሪያ፣ የምስራቅ ጐጃም ዞን ባህልና ቱሪዝም፣ የምዕራብ ጐጃምና አዊ ዞን ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤቶችን በማመስገን በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የቱሪስት መስህቦች የሚያሳየውን አውደ ርዕይ በይፋ ከፍተዋል፡፡

አውደ ርዕዩን የጎበኙ ተሳታፊዎች በጉብኝቱ ወቅት የተለያዩ የቱሪዝም መዳረሻዎችን ገላጭ በሆነ ፎቶ ግራፍ ማየት በመቻላቸው ዝግጅቱ የቱሪዝም መዳረሻዎችን ከማስተዋወቅ አንጻር የላቀ ሚና እንዳለው ተናግረዋል፡፡በዓሉ ሲከበር የቱሪዝምና ሆቴል ማኔጅመንት ትምህርት ክፍል መምህራንና ተማሪዎች የተለያዩ ስራዎችን ያቀረቡ ሲሆን ለአንድ ሳምንት የቆየ የፅዳት ዘመቻ፣ የእግር ኳስ ጨዋታ፣ የጥያቄና መልስ ውድድር፣ ተማሪዎች የመጡበትን አካባቢ የሚገልፅ የአለባበስ ትርኢት በማሳየት የእግር ጉዞ፣ የሴቶችና የወንዶች ፋሽን ሾው፣ የቁንጅና ውድድር፣ የሩጫ ውድድር እንዲሁም የፓናል ውይይት ተካሂዷል፡፡

## ኮሌጁ አውደ ጥናት አካሄደ

ሙሉጎጃም አንዱዓለም

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በእውቀት፣ በአመለካከትና በክህሎት የተገነቡ ብቁ የህክምና ባለሙያዎችን ለማፍራት በሚያደርገው ጥረት ላይ ደረጃውን የጠበቀ አዲስ ሆስፒታል ያስገነባ ሲሆን በሆስፒታሉ ዙሪያ አስፈላጊውን ግብዓት ለማሟላት በሴኔት አዳራሽ አውደ ጥናት አካሂዷል፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ ግንባታውን አስመልክተው እንደተናገሩት የሆስፒታሉ አሰራር (ዲዛይን) ሲነደፍ ከባለሙያዎች ጋር ሰፊ ውይይት በመደረጉ ደረጃውን የጠበቀ ሕንፃ መገንባት ተችሏል፡፡ አስፈላጊ ግብዓቶችን በአጭር ጊዜ ውስጥ በማሟላት ወደ ስራ ለመግባት ኮሌጁ በአውደ ጥናቱ ላይ የተጠቀሱትን በርካታ ሀሳቦች በመተግበር ሆስፒታሉን ስራ ማስጀመር እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ትኩረት ከሰጣቸው ስራዎች ዋናው የሆስፒታሉ ግንባታ መሆኑን ጠቅሰው ኮሌጁ በፈለገ ህይወት ሪፈራል ሆስፒታል አካባቢ የማስፋፋት ስራ እንደሚያከናውንና ተጨማሪ ግቢ እንደሚኖረው ፕሬዝዳንቱ ገልፀዋል፡፡

ሆስፒታሉ ከመማር ማስተማሩ ጐን ለጐን የሕክምና አገልግሎት ስለሚሰጥ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች እንደሚሟሉና በአጭር ጊዜ ወደ ስራው መግባት የሚያስችለውን የአሰራር ስልት እንደሚቀየስ በአውደ ጥናቱ ላይ በዝርዝር ቀርቧል፡፡

በአውደ ጥናቱ ላይ ከጤና ጥበቃና ከተለያዩ ቢሮዎች የመጡ ባለሙያዎች የተሳተፉ ሲሆን ሆስፒታሉን እውን ለማድረግ መሟላት የሚገባቸው ያሏቸውንና ከጉብኝቱ የተገነዘቡትን የገለጹ ሲሆን የህንፃ ተቋራጩ ላይ ክትትል ማድረግ እንደሚገባ፣ ለቤተ ሙከራ የተሰራው ክፍል ማሻሻያ እንደሚያስፈልገው አሳስበዋል፡፡

## አገር አቀፍ የምክክር አውደ ጥናት ተካሄደ

አምሳሉ ጥላሁን

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ «ጣናንና ግድቦቻችንን ከእንቦጭ አረም ጥፋት እንታደጋቸው» በሚል መሪ ቃል አገር አቀፍ የምክክር አውደ ጥናት አካሄደ፡፡

በአውደ ጥናቱ ላይ የተገኙት የአካባቢና ደን ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዲኤታ ክቡር አቶ ከበደ ይማም ጣና ሀይቅ በውስጡ ብዙ ተፈጥሯዊ ሐብቶችን በመያዙ ሐይቁን ከጥፋት ለመታደግ ክልሉና የፌደራል መንግስት በጋራ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድ ነድፈው መስራት እንደሚገባቸው ተናግረዋል፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያ በ2017 ዓ.ም መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለመሰለፍ ራዕይ አስቀምጣ እየሰራች እንደምትገኝና ለዚህ እቅድ ስኬት በግብርና፣ በትምህርት፣ በጤና፣ በተፈጥሮ ሐብትና በታዳሽ የሀይል ምንጭ እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮችን መንግስት አትኩሮት በመስጠት እየሰራ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

የእንቦጭ አረም በጣና ሐይቅ ላይ ከተከሰተበት ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከአካባቢው ህብረተሰብ መሪዎች እንዲሁም ከክልሉ መንግስት ጋራ በመተባበር ባደረጉት እንቅስቃሴ አረሙ እንዲቀንስ አድርገዋል፡፡ሆኖም ከዚህ በፊት የነበረው የማህበረሰቡ ንቅናቄ በ2006 ዓ.ም በመቀዝቀዙ አረሙ መልሶ መስፋፋቱን የተናገሩት የአማራ ክልል ርዕስ መስተዳድር ክቡር አቶ ገዱ አንዳርጋቸው የክልሉ መንግስት ችግሩን ለመፍታት ትኩረት ሰጥቶ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ የአገር አቀፍ የምክክር አውደ ጥናቱ አላማ በሐይቁ ላይ የተከሰተውን ችግር ለማስወገድ ባለሙያዎችን በማሰባሰብ መፍትሄ እንዲያመጡና ሌሎቹም አጋር አካላት በእውቀት እና በገንዘብ እንዲረዱ ጥሪ ለማስተላለፍ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዝዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው ዩኒቨርሲቲው በአሁኑ ወቅት የመማር ማስተማር፣ የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት ተልዕኮዎችን በመተግበር ላይ እንደሚገኝና የእንቦጭ አረም በጣና ሐይቅ በ2004 ዓ.ም በዩኒቨርሲቲው ተመራማሪዎች ከተለየበት ጊዜ ጀምሮ የአካባቢውን ማህበረሰብ በማስተባበር አመርቂ ስራ ተሰርቶ እንደነበር ነገር ግን በ2006 ዓ.ም ይህን የማህበረሰብ ንቅናቄ ይዞ መቀጠል ባለመቻሉ ችግሩ መልሶ እንዲከሰትና እንዲንሰራፋ እንዳደረገው ገልፀዋል፡፡ ወደፊትም በባሕር ዳር አካባቢ የሚከሰቱ ችግሮችን ለመፍታት ዩኒቨርሲቲው ጠንክሮ እንደሚሰራ ምክትል ፕሬዝዳንቱ ተናግረዋል፡፡

# አበይት ዜናዎች...

## ለሴት ተማሪዎች ስልጠና ተሰጠ

አበባ ሐብቱ

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከትምህርት ሚኒስቴር እና ሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር «የኢትዮጵያ ሴቶች ትግልና ድሎቻቸው» በሚል ርዕስ ለባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሴት ተማሪዎች የሁለት ቀን ስልጠና ሰጠ፡፡

የኢፌዲሪ ምክትል ዋና እንባ ጠባቂ ክብርት ወ/ሮ ሰራዊት ስለሺ እንዳሉት ሴት ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመግባት አቅም ከፍ ማድረግና ከገቡ በኋላም ስኬታማ ሆነው እንዲመረቁና የስኬታማ ሴት መምህራን ቁጥር ማብዛት አወንታዊ አስተዋፅኦ እንዳለው ገልጸው በተለይ በሴት ተማሪዎች ተሳትፎና ውጤታማነት ላይ አሁንም ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራበት የሚገባ ጉዳይ ነው ብለዋል፡፡ በፊት ላይ ለሴቶች ትምህርት የማህበረሰብ ድጋፍ ዝቅተኛ እንደነበረና ሴቶች በመሆናቸው ብቻ ችግር ሲደርስባቸው እንደነበረ ጠቅሰው ይህ ስልጠና ግንዛቤ በመስጠት በየመስኩ ሴቶችን በማብቃት የልማትና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ዋና ተዋናይ እንዲሆኑ መስራትና መደገፍ እንደሚስፈልግ እንዲሁም ሴት አመራሮችም ኃላፊነታቸውን በብቃት በመወጣት ለሴት ተማሪዎቻቸው አርአያ መሆን እንዳለባቸው ተናግረዋል፡፡

የአማርኛ ቋንቋ ማበልፀጊያ ተቋም ዳይሬክተር ዶ/ር ሂሩት ካሳው የስልጠናው አላማ ሴት ተማሪዎች ካሉባቸው ችግሮችና ተግዳሮቶች ተላቀው ውጤታማ እንደሚሆኑና ከቀደሙት አርአያ ከሆኑት ሴት ታጋዮች ተሞክሮ በመውሰድ ችግሮችን አሸንፈው ለውጤት እንዲደርሱ ግንዛቤ ለመፍጠር እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

በስልጠናው ወቅት የኢትዮጵያ ሴቶች ትግል እና የሕዳሴ ጉዞ ገጽታዎችን፣ የሴቶች የፀረ ጭቆና ትግል፣ የኢፌዲሪ ሕገመንግስት ከሴቶች አኳያ፣ ሕገ መንግስታዊ ቱርፋቶች እና ተግዳሮቶች የሚሉ የመነሻ ፅሁፎች የቀረቡ ሲሆን ሴት ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በሚያጋጥሟቸው ችግሮች ላይ ሰፊ ውይይት ተካሂዷል፡፡

ስልጠናው የተሰጠው በዩኒቨርሲቲው አምስት ግቢዎች ሲሆን ተሳታፊ ተማሪዎች ከሴት ታጋዮች ጠቃሚ ተሞክሮ እንዳገኙ እና በግቢ ቆይታቸው የተለያዩ ተግዳሮቶች ቢኖሩም ችግሮችን ተቋቁመው ለውጤት ለመብቃት የሚያስችላቸውን በቂ ግንዛቤ እንዳገኙ ተናግረዋል፡፡ ወደፊት ያለባቸውን ችግሮች ከዩኒቨርሲቲው ጋር ግልጽ ውይይት በማድረግ መፍታት እንዲችሉ የጋራ መግባባት ላይ መደረሱን ተናግረዋል፡፡

## ዩኒቨርሲቲው የዘር ብዜት ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑ ተገለጸ

ታድየ አስማረ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የተቀናጀ የዘር ዘርፍ ልማት (አይ.ኤስ.ኤስ.ዲ) የክልሉ ግብርና ቢሮና የዩኒቨርሲቲው ኃላፊዎች፣ ዘር አባዥ ድርጅቶች፣ የቀጥታ ግብይት ማህበራት እና የዘርፉ ባለሙያዎች በተገኙበት የሥራ እንቅስቃሴውን ለመገምገም በዳንግላ ከተማ የአንድ ቀን አውደ ጥናትና በተመረጡ የአዊና የምዕራብ ጎጃም ዞኖች የመስክ ጉብኝት አካሄደ፡፡

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ ኃላፊ ዶ/ር ተሾመ ዋለ አውደ ጥናቱን ሲከፍቱ የተቀናጀ የዘር ዘርፍ ልማት (አይ.ኤስ.ኤስ.ዲ) የአማራ ፕሮግራምና አጋር ድርጅቶችን በዘር ብዜት ላይ ትኩረት ሰጥተው በመስራታቸው ዘርፉን ለማሳደግ እንደቻሉና የነዋሪውን የአኗኗር ደረጃ መሻሻሉን ገልጸው ይህን ስራ ለማጠናከር መንግስት የግል ዘርፉን ማበረታታትና የአቅም ግንባታ ስልጠና በመስጠት ተግባራዊ ማድረግ እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

በአውደ ጥናቱ ላይ የምርት ብዜትና የቀጥታ ግብይት ሂደት ላይ የተገኙ ውጤቶችና ያጋጠሙ ችግሮችና የወደፊት አቅጣጫዎች ላይ ውይይት ተደርጓል፡፡ የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች እየተሰራ ያለውን ስራ የጎበኙ ሲሆን የተቀናጀ የዘር ዘርፍ ልማት ፕሮግራም (አይ.ኤስ.ኤስ.ዲ) እየሰራ ያለውን ስራ አድንቀዋል፡፡

የተቀናጀ የዘር ዘርፍ ልማት ፕሮግራም (አይ.ኤስ.ኤስ.ዲ) በኔዘርላንድ መንግስት የሚደገፍ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር በአማራ ክልል የተለያዩ ወረዳዎች የዘር ብዜት ጥራትና ስርጭት ላይ እየሰራ ይገኛል፡፡ የተቀናጀ የዘር ዘርፉ ልማት በምርጥ ዘር ማባዛትና የቀጥታ ዘር ግብይት የሚሠራ ሲሆን አላማው በአካባቢው የተሻሉ የሀገር በቀል ዘሮችን መርጦ ለአርሶ አደሩ በተፈለገው ጊዜ እና ቦታ በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ዘርፉን ማሳደግና ከዘርፉም የአርሶ አደሩ አኗኗር የተሻለ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ በዚህ ፕሮግራም ታቅፈው በአጋርነት የሚሠሩ የግል ዘር አምራች ድርጅቶች፣ በዘርና ግብይት ሥራ የተሰማሩ የአካባቢው ገበሬዎች ማህበራት፣ የግልና የመንግስት ባለሙያዎች ናቸው፡፡

## የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎች ተጎበኙ

ታድየ አስማረ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምር እና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት በሜጫ ወረዳ ቆለላ ገጠር ቀበሌ ያከናወናቸውን ዘርፈ ብዙ ሥራዎች ለተወካዮች ምክር ቤት የሰው ሃብት ቋሚ ኮሚቴ አባላት እና ለአማራ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊዎች አስጐበኙ፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው በጉብኝቱ ወቅት ዩኒቨርሲቲው ለአካባቢው የገጠር ቀበሌዎች ዘርፈ ብዙ የማህበረሰብ አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝና አርሶ አደሩ ያለውን የተፈጥሮ ሀብት በመጠቀም በልማቱ ይበልጥ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል ሞዴል የገጠር ቀበሌዎችን በመፍጠር በመስራት ላይ እንዳለ ገልጸዋል፡፡ ዶ/ር ተስፋዬ በቆለላ ሞዴል ገጠር ቀበሌ የትምህርት ቤት ግንባታ፣ የውሃ ግንባታ፣ በተፈጥሮ ጥበቃ፣ በንብ ማነብ ስራ፣ በጤና አጠባበቅ እና የጐጂ ባህል አወጋገድ ላይ ባለሙያዎችን በመላክ እውቀታቸውንና ልምዳቸውን በማካፈል አርሶ አደሩን ተጠቃሚ ለማድረግ መቻሉን ተናግረው ይህ ስኬታማ እንዲሆን የዩኒቨርሲቲው መምህራን በፈቃደኝነት ያለክፍያ በመስራታቸው ሊመሰገኑ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው የማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክተር ዶ/ር ጌታቸው ፍስሃ እንደገለፁት በመንደሩ ያለው ትምህርት ቤት ያለበትን ችግር በማጥናት ለት/ቤቱ ተጨማሪ አራት ክፍሎች በማስገንባትና በማደስ የመማሪያ ክፍሎች ችግር እንዲቀረፍ መደረጉንና የትምህርት ቁሳቁሶችን ማሟላት መቻሉን ተናግረዋል፡፡

በቆለላ የሶላር መንደር ሞዴል ፕሮጀክት አስተባባሪ አቶ ምንይችል ግታው ለጎብኚዎቹ እንደገለጹት ዩኒቨርሲቲው ከአርሶ አደሩ ጋር በመተባበር ውሃ ከጉድጓድ በመሳብ ወደ አርሶ አደሩ መኖሪያ አቅራቢያ ለማድረስ አነስተኛ የሶላር ቴክኖሎጂን በመጠቀም የኤሌክትሪክ ኃይል በማመንጨትና የውሃ መሳቢያ ሞተር እንዲተከል በማድረግ አርሶ አደሩን የንፁህ ውሃ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህ ረገድ ማህበረሰቡን የንፁህ ውሃ መጠጥ ተጠቃሚ ከማድረግ ባሻገር ሴቶች ውሃ ለመቅዳት ከመኖሪያ ቤታቸው ርቀው ሲሄዱ ይደርስባቸው የነበረውን ችግር ለመቀነስ ተችሏል፡፡

የአካባቢው ነዋሪዎች ዩኒቨርሲቲው በቀበሌው ላይ እየሰራ ያለውን ስራ ለእንግዶቹ የገለጹ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው ያለባቸውን ችግሮች በመለየትና ለመቅረፍ ስላደረገው ዘርፈ ብዙ ሥራዎች እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ከፍተኛ ምስጋና አቅርበው ወደፊትም የበለጠ ለውጥ እንዲመጣ ዩኒቨርሲቲው ከጐናቸው እንደሚቆምና ድጋፍ እንደሚያደርግላቸው ትልቅ ተስፋ እንዳላቸው ተናግረዋል፡፡

የጉብኝቱ ተሳታፊዎች ዩኒቨርሲቲው በአርሶ አደሩ መካከል በመገኘት የአኗኗር ዘዴው እንዲሻሻል ለማድረግ እየሰራ ያለው ተግባር የሚበረታታ መሆኑን በመገለጽ አርሶ አደሩ በስራዎቹ የባለቤትነት ስሜት ተሰምቶት ንብረቶቹን እንዲጠብቅ የግንዛቤ ስራ መሰራት እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው የማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በአካባቢው ላይ በባለሙያዎች ተጠንቶ በተሰጠው ግብአት መሰረት የተራቆቱ መሬቶችን ችግኝ በመትከል፣ ለመምህራን የሙያ ማሻሻያ ስልጠና በመስጠት፣ ሴቶች የኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የገቢ ማስገኛ ስራዎች ላይ ስልጠናና ድጋፍ በማድረግ፣ የዘመናዊ የንብ ቀፎ አመራረትና የንብ ማነብ ስልጠና በመስጠት እና ወደ ሥራው እንዲገቡ በማገዝ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል፡፡ የጐጂ ባህል ማስወገድ፣ በጤና አጠባበቅ፣ በሴቶች እኩልነት፣ ህፃናትን ወደ ትምህርት ቤት መላክ የሚያስገኘው ጥቅም ላይ ትኩረት ተሰጥቶ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችንም እየሠራ ይገኛል፡፡ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ስራዎች በዩኒቨርሲቲው በጐ ፈቃደኛ መምህራን እየተሰሩ ያሉ ሲሆን ስራዎቹ ወደ ገንዘብ ሲመነዘሩ ወደ 1.7 ሚሊየን ብር ይገመታሉ፡፡

## ለዩኒቨርሲቲ ሰራተኞች ስልጠና ተሰጠ

ትዕግስት ዳዊት

ለባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ሰራተኞች በአገሪቱ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ዙሪያ ለሰባት ተከታታይ ቀናት በባለሙያዎች ስልጠና ተሰጠ፡፡ በስልጠናው ላይ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አጭር የትግል ታሪክ፣ አገራዊ ህዳሴያችንና ፈተናዎቹ፣ ህገ-መንግስታዊ መርሆዎች፣ ዓለማዊ ትምህርትና ልማታዊ የመንግስት ሰራተኛ የመገንባት አስፈላጊነት በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት ተደርጓል፡፡

በስልጠናው ላይ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤና ሌሎች ከፍተኛ አመራሮች የተገኙ ሲሆን ዶ/ር ባይሌ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተልዕኮ፣ ስኬትና ተግዳሮቶች እና የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2025 ለመድረስ ያቀደውን ዕቅድ እንዴት ማሳካት እንደሚቻል ለስልጠናው ተሳታፊዎች በዝርዝር አቅርበዋል፡፡

የስልጠናው ተሳታፊዎችም የቀረቡትን ጽሁፎች መነሻ በማድረግ ከሀገሪቱና ከዩኒቨርሲቲው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ የተለያዩ ሀሳቦችንና ጥያቄዎችን ያነሱ ሲሆን የጥያቄዎቻቸው ምላሾች በአጭር፣ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ ዕቅዶች ውስጥ ተካተው ተግባራዊ እንዲሆኑ ጠይቀዋል፡፡ በስልጠናው ማጠናቀቂያ ላይ ተሳታፊዎች የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2025 አፍሪካ ውስጥ ካሉ ምርጥ 10 የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች መካከል አንዱ ለመሆን ያለውን ራዕይ ለማሳካት በጋራ እንደሚሰሩ ገልጸዋል፡፡

# ‹‹ቁጭ ብለን የሰቀልነውን ቆመን ማውረድ አቃተን›› አባ መላ አባ መቻል

በታምሩ ደለለኝ

የሳይኮሎጂ ት/ት ክፍል ባልደረባ

በአንድ ወቅት አንድ ሰው አንዲት ሴተኛ አዳሪን ለአንድ ሌሊት ሁለት ብር እከፍልሻለሁ ብሎ ከቤቱ ያሳድራታል፡፡ ከዚያም ነገርዋ ጣፈጠው መሰል እቤቱ አስቀራት፡፡ ከአምስት አመት በኋላ ግን የአዲስ ሰው ነገር ያምረውና ጥፊልኝ ይላታል፡፡ አጅሪት ግን ‹‹አምስት አመት ሙሉ ከኖርኩበት ቤቴ ወዴት ነው የምሄደው?›› አለች፡፡ ‹‹መሄዴ ግድ ከሆነም አብሬህ ያፈራሁትን ንብረት ተካፍዬ ነው!›› ስትል ብስጭቷን ትገልፃለች፡፡ ‹‹ደግሞ ሴተኛ አዳሪ ከመቼ ጀምሮ ነው ቤት ንብረት መካፈል የጀመረችው?›› በማለት በሰላም እንድትሄድ ያስጠነቅቃታል፡፡ ሴትየዋ ግን አልሰማህም ብላ ከአጤ ምኒሊክ ትከሳለች፤ አባ ዳኘውም ‹‹... ሰማንያ ከሌለሽ ልትካፈይ አትችይም›› ብለው የባሏን ሃሳብ ደገሙላት፡፡ እሷ ግን የአባ ዳኘውን ፍርድ ሳትቀበል ለሐብቴ ይግባኝ ትላለች፡፡ በይግባኝ ችሎት ላይ ባልየውም አላካፍልም ማለቱንና መብቱም እንደሆነ በሙሉ ልብ ለሐብቴ አረጋገጠ፡፡ ሐብቴም በጽሞና ከሳሽና ተከሳሽን ካደመጡ በኋላ ‹‹አዬ ጉድ አዬ ጉድ የሴት ነገር የጋብቻ ውል ሳይኖር ንብረት አካፍሉኝ ማለት፡፡ እውነትም ተበድለሃል፡፡ አታካፍልም፡፡ ነገር ግን ለአምስት አመት አሳድረሃታልና ለአንድ ሌሊት ሁለት ብር በታሰበ ትከፍላታለህ›› ብለው ፈረዱ፡፡ ወንድማችን ታዲያ ሒሳቡን ቢያሰላው 3650 ብር ሆነበት፡፡ አይደለም አካፍሎ ሙሉ ንብረቱን ቢሠጣትም ይሄን ስለማያወጣ እህታችንን በሰማንያ አግብቶ ትዳሩን አከበረ፡፡ ከላይ ባየነው የፍትሃ ብሔር ጉዳይ የሃገሪቱ ንጉሰ ነገስት የሰጡትን የመጨረሻ ብይን ታልፎ ይግባኝ የሚባልባቸው ሐብቴ የተባሉት ሰው ኧረ ማናቸው?

በዛሬው ጹሑፌ ትኩረት የማደርገውም በእኝሁ በአጤ ምኒሊክ (አባ ዳኘው)፣ በልጅ እያሱ (አባ ጤና)፣ በንግስት ዘውዲቱ (ማሚቴ) እና በንጉስ ተፈሪ መኮንን (ንጉሰ ነገስት ቀዳማዊ ሐይለ ሥላሴ ከመሆናቸው በፊት) ዘመን ሀገራችንን ከ30 አመት በላይ እጅግ ተፈርተውና ተከብረው በጦር (በመከላከያ) ሚኒስትርነት ያገለገሉትን ጌታ ፊታውራሪ ሐብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴን ማንነት በአጭሩ ማስተዋወቅ ላይ ነው፡፡ ስለሳቸው አንዳአንድ ነገር እንድል ያነሳሳኝ በማንኛውም እድሜ ላይ ለምንገኝ ዜጎች አርአያ የሚሆን ጥበብና ማንነት ስለነበራቸው ነው፡፡ ትዕግስት፣ ጠልቆ ማሰብ፣ ታታሪነት፣ ለሀገርና ለመንግስት ታማኝና ታዛዥ መሆን፣ የሀገር ፍቅርና ብሔራዊ ኩራት ከሳቸው የህይወት ታሪክ በጥቂቱ የምንማራቸው ቁነገሮች ናቸው፡፡ ከላይ የጀመርኩበትም ቀልድ መሰል ቁምነገር ሐብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ በተቀመጡበት ችሎት የሰጡት ብይን ነበር፡፡ እነሆ ሐብቴ ዲነግዴ፡-



## ትውልድና እድገት

እኚህ ስመጥር ኢትዮጵያዊ የጦር ሚኒስትር የትና ከማን እንደተወለዱ፣ በማን ስር እንዳደጉ፣ ወላጅ ያወጣላቸው ስም እንኳን ሳይቀር የተቀመጡት የታሪክ መረጃዎች የተምታቱ ናቸው፡፡ አቶ ታቦር ዋሚ በጀግናው ገርሱ ዱኪ (አባ ቦራ) ህይወት ላይ በሚያጠነጥነው መጽሐፋቸው ውስጥ ሐብቴ ዲነግዴ የተወለዱት ከአባታቸው አቶ ዲነግዴ ሁንዱል እና ከሰባት ቤት ጉራጌ ከሚወለዱት እናታቸው ባርሴማ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ የአባታቸውን ብሔር ግን አልገለጹም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ስማቸው ለምን እንተቀየረ ባያስረዱም ወላጆቻቸው ያወጡላቸው ስም ግን ‹‹ቁሴ›› እንደነበር ታቦር ዋሚ ጠቅሰዋል፡፡

ይህንን የአቶ ታቦር ዋሚ የአባት ብሔርና የስም ለውጥ ምክንያት ያለመጥቀስ ክፍተት በተወሰነ መልኩ የሚያሟላ የሚመስል ጹሑፍ በቀኝ አዝማች ታደሰ ዘወልዴ “ፊታውራሪ ሀብተጊዮርስ (አባ መላ): 1844-1919” በሚለው መጸሐፍ ውሰጥ ይገኛል፡፡ ይህም አባታቸው አቶ ዲነግዴ ኦሮሞ እንደነበሩ (በርግጥ ዲነግዴ ማለት በኦሮሞኛ በግርድፉ ምጣኔ ሀብት ሲሆን እንደሳቸው የተማረከው ታናሽ ወንድማቸው ስምም ገዳ ይባል ነበር) እንዲሁም ስማቸው ሐብተጊዮርጊስ የሆነው በጉረምስና ዘመናቸው በምኒሊክ ሰራዊት ከተማረኩ በኃላ በአንኮበር ጊዮርጊስ የተሠጣቸው ስመ ጥምቀት ፀንቶ በመቅረቱ ምክንያት መሆኑ ተገ ልጿል፡፡

እንደ እኔ እይታ የአባታቸውን ብሔር ማወቁ ፋይዳው ያን ያህል ጎልቶ ባይታየኝም ነገር ግን አንባቢው የእናታቸውን ሲያይ የአባታቸውስ ምንድን ነው ብሎ ለሚያነሳው ጥያቄ እረፍት ለመስጠት ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ባነበብኳቸው መጽሐፍት ውስጥ የእናታቸው የብሔር ማንነት ተደጋግሞ ስለተጠቀሰ ከጠቀሱ አይቀር ፀሐፊያን ያባታቸውንም በመጠቆም የተሟላ ቢደርጉት ብዬ ነው ፡፡

የትውልድ ስፍራቸውን በተመለከተ እንደ ታቦር ዋሚ ከሆነ ሐብቴ የተወለዱት በደንዲ ወረዳ ቦዳ ምክትል ወረዳ ልዩ ስሙ ጊንዶ በተባለው ቦታ ነው፡፡ በሌላ በኩል አምባሳደር ዘውዴ ረታ ‹‹ተፈሪ መኮንን፡- ረጅሙ የስልጣን ጉዞ›› በሚለው መጽሐፋቸው ጠቅለል ባለ መልኩ ታዋቂዎችን የታሪክ ፀሐፊያን ተክለ ፃዲቅ መኩሪያንና ብላቴን ጌታ ማህተመስላሴ ወ/መስቀልን ጠቅሰው እንደፃፉት ሐብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ የተወለዱት የጨቦና ጉራጌ ተወላጆች ከሆኑት አቶ ዲነግዴና ከእመት አርሴማ (በታቦር ዋሚ ግን ‹‹ባርሴማ››) በ1844 ዓ.ም እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ እንደተወለዱም እናታቸው ያወጡላቸው ስም ሐብቴ እንደሆነ እና በ40 ቀን ክርስትና ሲነሱ ቄሶች የመጸሀፍ ስማቸው ሐ/ጊዮርጊስ ብለው ከሰየሙ በኃላ በዚሁ መጠራት እንደቀጠለ አያይዘው ጽፈዋል፡፡ እንደ ‹‹ያልተዘመረላቸው›› መጽሐፍ ደራሲ ፍጹም ወልደ ማርያም ከሆነ ምንም እንኳን የእነ ተክለጻዲቅ መኩሪያ እምነት የብዙ ጻሐፍት ስምምነት መሆኑን እውቅና ቢሠጥም የሌሎች ፀሐፊያን እምነት ግን የሐብቴ ዲነግዴ እናትና አባት ስም እንዲሁም የትውልድ ስፍራ ከላይ ከተቀመጠው ይለያል፡፡ ሐብቴ የተወለዱት ከአባታቸው ዲነግዴ ቦተረ (በታቦር ዋሚ ዲነግዲ ሁንድል ሲሆን) እና ከእናታቸው ኢጁ አመዲና (ባርሴማም ሆነ አርሴማም ሳይሆን) በሸዋ ክፍለ ሀገር ጁባትና ሜጫ አውራጃ በደንዲ ወረዳ በቦዳና ቀበሌ ምክትል ወረዳ ቱቃ ገንዲ ቀበሌ የደንዲ ወንዝ ከሚመነጭበት ውብና ለምለም ስፍራ በ1844 እንደሆነ አትቷል፡፡ የትውልድ ስፍራቸው አቶ ታቦር ዋሚ ካስቀመጡት ጋር አንድ አይነት ሲሆን ነገር ግን ሌተና ኮሎኔል አበባ ወ/ተንሳይ በሀገራችን ወታደራዊ ታሪክ ላይ በሚያተኩረው ‹‹ቀሰና ጦርሠ.›› በሚለው መጽሐፋቸው ካስቀመጡት የጨቦና ጉራጌ አውራጃ ወሊሶ ወረዳ አመያ ግን ይለያል፡፡ ዞሮ ዞሮ ሐብቴ ዲነግዴ ያገለገሉት በጣም ካጠበብነው የሸዋን የራስ ገዝ አስተዳደር መንግስት (Autonomous Regional State) አሰፍተን ካየነው ደግሞ ኢትዮጵያን ነውና ጅባትና ሜጫ አውራጃ ሆነ ጨቦና ጉራጌ ያው ሸዋና ኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚገኙ ሰውየው የተወለዱት በጠባቡ ሸዋ ውስጥ በሰፊው ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ ነው ብዬ መገላገል ፈለግኩ፡፡ ማን አስገደደህና ቀድሞውንስ እንዳትሉኝ ብቻ? ለማንኛውም የታሪክ ምሁራን ግን ቀዳዳውን ለመድፈን የበኩላችሁን ጥናት ብታደርጉ ጥሩ ነው እላለሁ፡፡

ልክ እንደስማቸው፣ ትውልድ ስፍራቸው እና ብሔራቸው ሁሉ የአስተዳደጋቸውም ሁኔታ እንዲሁ አወዛጋቢ ነው፡፡ በልጅነታቸው በምርኮ ተወስደው ከእናትና አባት ውጭ ከማደጋቸው በቀር፤ በጸሀፍት መካከል ስምምነት አይነበብም፡፡ ምርኮውም የመጣው የአፄ ምኒሊክ መንግስት መላው የሸዋን ግዛት አዋህዶና አንድ አድርጎ የማስተዳደሩን አላማ ለማስፈጸም በራስ ጎበና ዳጩ (አባ ጥጉ) መሪነት ካካሄዳቸው ዘመቻዎች በአንዱ ነው፡፡ እንደ ፍጹም ወለደ ማርያም ጹሑፍ ከሆነ በወቅቱ ወደ ጅባትና ሜጫ አውራጃ በዘመተው የራስ ጎበና ጦር ውስጥ በነበሩት አቶ አይተንፍሱ የተባሉ ወታደር (ሌሎች ምንጮች ከራስ ጉበና ጦር ውስጥ በነበሩ የጅሩ ተወላጅ ጭፍሮች በሆኑት በአቶ ጋረደው አባተ ምሳስ አልያም በአቶ አጥናፌ ቀርሾ) ፈሊጦ ከተባለው ዋሻ አቅራቢያ ከሚገኘው የእህታቸው ቤት ውስጥ ተሸሽገው የነበሩት ትንሹ ሐብቴ ተማርከው ከተወሰዱ በኃላ ወታደሩ እንደ ልጃቸው በጥሩ እንክብካቤ እንዳሳደጎቸው ነው፡፡ ሐብቴም በበኩላቸው ባይወልዷቸውም እንደ አባት ያሳደጓቸውን አቶ አይተንፍሱን ከእድሜ እኩዮቻቸው በላቀ መልኩ ጥንካሬያቸውን በእርሻ ሥራ፣ በፈረስ ግልቢያ፣ በጦር ውርወራና የጋሻ ምከታ ስልት በማሳየት ያኮሯቸው እንደነበር ፍጹም ወ/ማርያም አክሏል፡፡ ይህ አካላዊ ጥንካሬያቸውና ክህሎታቸው በተፈጥሮ ከተቸራቸው ነገሮችን ፈጥኖ ከሚረዳው መስተዛላያቸው ጋር ተዳምሮ አሳዳጊ እናታቸውን ወ/ሮ ባፈናን ከአሳዳጊው አባታቸው አቶ አይተንፍሱን በተቃራኒ መንገድ ለሰይጣናዊ ተግባር አሳልፏቸው ነበር፤ ምንም እንኳን በአቶ አይተንፍሱ ቢከሽፍም፡፡ ሰይጣናዊው ምኞትም የመጣው የሐብቴ ጥንካሬና ንቁ አይምሮ ወደ ሌላ ወታደር (ነፍጠኛ) እንዳይሄድ ከመፍራት ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ወይዘሮ ባፈና የጓያ እሸት በወተት በማብላት እግሩ እንዲሽመደመድ በማድረግ ዘላለሙን በእርሻ ስራ ቤታቸውን እንዲያገለግል ለማድረግ ነበር፡፡ ምኒሊክ ኋላ ላይ ‹‹ሐብተጊዮርጊስ አንደ ብቻ ሆነብን እንጂ›› ብለው የሳሱላቸውን ‹‹ጂኒየስ›› እሜቴ ጭራሽ ዜሮ አድርገውላቸው ነበር፡፡ ለማንኛውም ወደ ጀመርኩት ልመለስና ‹‹አዋጅ ... አዋጅ... አዋጅ... የጨቦን ሰው ማርከህ እቤትህ ያስቀመጥህ ወደኔ አምጣ፡፡ ሳታመጣ ቀርተህ በአውጫጭኝ የተገኘህ ርስትህን ትነጠቃለህ›› ሲባል ነበር የመጀመሪያው የሐብቴ የእድል በር ገርበብ ብሎ የተከፈተው፡፡ ምክንያቱም ጉዞ ወደ ቤተ-መንግስታዊ ህይወት ተጀመረ፡፡ በአዋጁ ምክንያት ወራሻቸው ለማድረግ ይመኙት የነበረውን ልጅ ለአፄ ምኒሊክ እየሳሱ አቶ አይተንፍሱ አስረከቡ፡፡ በዚህ አዋጅ መሠረት መቼስ የጅባትና ሜጫ ምርኮኞች አልተጠሩ ይሄንንም አዋጅ መነገሩን የፃፈልን ፍጹም ወለደማርያም ታዲያ ሐብቴ ከጨቦ ና ጉራጌ እንዳልተማረኩ ነግሮን ሲያበቃ አቶ አይተንፍሱም ካልተገደዱ በቀር ለማንም እንደማይሰጡ ነግሮን እያለ እንዴት ታዲያ ለምኒሊክ አስረከቡ ይለናል? ፍጹሜ ክፍተቱን ለመዝጋት የሚያስችል ማስረጃ ብታቀርብልን ጥሩ ነው እላለሁ፡፡ ለግዜው ግን በቀኝ አዝማች ታደሰ ዘወልዴ መጸሐፍ ላይ ያገኘሁት መረጃ በአዋጁና በትውልድ ቦታቸው መሀል ያለውን ክፍተት የሚያጠብ ይመስለኛል፡፡ በቀኝ አዝማች ታደሰ ትንታኔ መሠረት ፊታወራሪ የተወለዱት በጨቦና ጉራጌ አውራጃ ጠረፍ በአመያና ወሊሶ ወረዳ ሲሆን በጅባትና ሜጫ አውራጃ በቦዳ ቀበሌ ግን ያሳለፉት ከ 7ዓመት እድሜያቸው እስከ 14 አመታቸው ድረስ በእህታቸው ቤት ሳሉ መሆኑን ይጠቁመናል፡፡ ሆኖም ሐብቴ ምናልባት ከጅባትና ሜጫ ለማረካቸው ወታደር ከላይ የተጠቀሰውን የትውልድ ቦታቸውን ምናልባት ስለገለፁ ሊሆን ይችላል በጨቦ አዋጅ ለሚኒሊክ የተሠጡት እያልኩ ከምርኮ በኋላ በማን ስር አደጉ ወደሚለው ሁለተኛው አማራጭ ትንታኔ ልለፍ፡፡ ይሄኛው አማራጭ በዘወዴ ረታ መጽሐፍ ውስጥ ሐብቴ በራስ ጎበና ምርኮ ከተወሰዱ በኋላ ያደጉት በአቶ አይተንፍሱ ቤት ሳይሆን የምኒሊክ አባትና አያት መዲና በነበረችው አንኮበር ከተማ በሚገኘው ቤተ-መንግስት ውስጥ በወህኒ አስተዳደሪው አዛዥ ወልደ ጻዲቅ ቤት ነው የሚል ነው፡፡ የአዛዥ ወልደ ጻዲቅ ሆነ የአቶ አይተንፍሱ ቤት ነፍጥ ያነገበ (የወታደር) ቤት ነውና ሐብቴን ወደፊት ለሚጠብቃቸው የጦር ሚኒስትርነት ሚና የሚያስፈልጋቸውን

ወደ ገጽ 12 የዞረ

# እንግዳ

በሂሩት አድማሱ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነጽሁፍ ት/ክፍል - የስነጽሁፍ መምህርት

nanihira@gmail.com

ልታገባ ነው፡፡ የሠርጓን ቀን እንደምጥ ተጨንቃ ስትጠባበቅ ቆይታለች፡፡ በፍርሃትና በደስታ ባህር ከግራ ቀኝ እየተላጋች ቀኑን በናፍቆት ስትቆጥር ቀኑ ደረስኩ እያለ ቀረበ፡፡ የምታገባው በጣም የምትወደውን ሰው ነው፡፡ ትውውቃቸው ከተራ የክፍል ጓደኝነት ወደ ፍቅረኝነት ያደገ በመሆኑ በምታገባው ሰው ያላት መተማመን ከፍ ያለ ነው፡፡ ፈፅሞ አትጠረጥረውም፣ የሷ ብቻ የዘላለሟ እንደሆነ ካመነች ቆይታለች፡፡ በሠርግ ማግባት የፈለገችው ከፍቅረኛዋ ጋር አንድ የምትሆንበትን ቀን ከጓደኞቿ እና ከምታከብረው የወደፊት ባሏ ጋር በደስታ ለማሳለፍ ልዩ የምትለውን ቀን በልዩ ዝግጅት ለመቀበል ነው፡፡

ሳምሶም ጠይም ቁመቱ መካከለኛ፣ ወንዳ ወንድ ፀጉሩ ለስለስ ያለ ሲያዩት የማይስብ ሲቀርቡት ግን የሚወደድ ባህሪ ያለው ጐልማሳ ነው፡፡ ከእሌኒ ጋር የተዋወቁት ዩኒቨርሲቲ የአንደኛ ዓመት ተማሪዎች ሆነው ነበር፡፡ በአንድ የትምህርት መስክ ውስጥ ተመድበው በመጀመሪያ ቀን በአጋጣሚ አጠገብ ላጠገብ በመቀመጣቸው በተፈጠረ ትውውቅ ግንኙነታቸው ከቀን ወደ ቀን እያደገ ከፍ ያለ ደረጃ ደረሰ፡፡ እሌኒ ሲበዛ አይናፋር ብትሆንም በሳምሶም ደፋርነት ተስባ ነገሮችን አጣፍጦ በማቅረብ ችሎታው ተማርካ ስለሱ በማሰብ ብዙ ሌሊቶች አሳልፋለች፡፡ በአንደበተ ርቱዕነቱ እንዲሁም ጥንካሬውን በሚያሳይ ሰውነቱ ተማርካ በምናቧ ብዙ ጊዜ ተመልክታዋለች፡፡ በሱ ሀሳብ መያዟን ስታስተውል ‹እንዴ ምን መሆኔ ነው?› ብላ ደንግጣ ሀሳቧን ለመሰብሰብ ሞክራለች፡፡ ይሁን እንጂ አዕምሮዋ እሱን ካለማሰብ የሚያርፈው ተገናኝተው በክፍል የተማሩትን፣ የተሠጣቸውን የቤት ሥራ አብረው ለመስራት በሚሞክሩበት ጊዜ ብቻ ነበር፡፡

“እሌኒ እንውጣ፡፡” እንጂ ጓደኛዋ ኤልሳ ነበረች ከሃሳቧ ያነቃቻች፡፡ የተከራዩትን ቬሎ ለማምጣት ተቃጥረው ወደዚያ ለመሄድ እቅድ ነበራቸው፡፡ “እሺ እንሂድ፡፡ በነገራችን ላይ አባዬ ለጉዳይ እንደሚመጣ ነገረኝ ከብዙ ጊዜ በኋላ ከአባቴ ጋር በአካል ልገናኝ ነው፡፡”

“በጣም ዳስ ይላል እና እንደምታገቢ ነግረሻቸዋል?”

“አልነገርኩትም”

“ምን ሆነሽ ነው?”

“የምልሽ ከአይን የራቀ  ከልብ የራቀ ነው፡፡ አልመጣልኝም፡፡”

“በይ በይ አትቀልጂ፡፡ ልትነግሪያቸው ይገባል”

“አባቴ ከልጅነቴ ጀምሮ ተቆራጭ እየሰጠ ቢያሳድገኝም በህይወቴ የሚሆነውን ነገር እየዘረዘርኩ ለመናገር የሚያስችል ቅርርብ የለንም፡፡ እሱም እንደ አባትነቱ ገንዘብ ከመላክ ውጭ ለእኔ ፍቅር ያለው አይመስለኝም”

“ቢሆንም ምንም ሳይቸግርሽ እንድትማሪ በማድረጋቸው ያለሽበትን ሁኔታ ማወቅ የግድ ይገባቸዋል፡፡”

“እሺ ባሕር ዳር እንደገባ ነግሮኛል፡፡ ስለ ሠርጌ ሳገኘው እነግረዋለሁ፤ ጊዜ አለኝ አይመስልሽም?”

“ይሻላል”

መንገድ ጀምረው ታክሲ ለመያዝ በመጠበቅ ላይ እንዳሉ የእሌኒ ስልክ አቃጨለ፤ ሳምሶም ነው፡፡

“ሄሎ”

“የኔ ቆንጆ … የት ነሽ”

“ከኤልሳ ጋር ቬሎውን ለማምጣት እየሄድኩ መንገድ ላይ ነኝ፡፡”

“ዛሬ ላግኝሽ?”

“ከቬሎው መልስ ከሰዓት በኋላ ይቻላል፡፡”

“ቤትሽን በቶሎ አስተካክይ የማስተዋውቅሽ እንግዳ አለ፡፡”

> “ትዳሬ እንዳይበተን እናንተ ልጆቼ እንዳትጠሉኝ በመፈለጌ ነበር ታሪኬን የሸሸኩት፡፡ ግን ምንም ነገር ተደብቆ አይቀርም፡፡ በስውር የተሰራ በገሃድ በአደባባይ አንድ ቀን ይጋለጣል፡፡”

“እንግዳ?! ልመለስ እንዴ?”

“ኧረ ትደርሻለሽ?”

“እሺ! የኔ ፍቅር ታዛዥ ነኝ፡፡”

እሌኒ ከኤሌሳ ጋር የተከራየችውን ቬሎ ካመጣች በኋላ ቤቱን ከኤልሳ ጋር እየተረዳዱ አዘጋጁት፡፡ ከሳምሶን ጋር በትዳር አብረው ለመኖር ከወሰኑ በኋላ የተከራዩት ቤት ትልቅ ሳሎን፣ ሁለት የመኝታ ክፍሎች፣ ሻወርና ማብሰያ ክፍል ያለው ነው፡፡ ትልቁ ቤት በእሌኒ ባለሙያነት እጅግ ተውቦ በሚማርክ መልኩ ተይዟል፡፡ የሶፋው፣ የምግብ ጠረጴዛው አቀማመጥ አይን ያፈዛል፡፡ በሳሎኑ ግርግዳ ላይ ከተሰቀሉት ተፈጥሮን ከሚያሳዩ ስዕሎች በተጨማሪ እሌኒ በጣም የምትወዳት የእናቷን ፎቶግራፍ ሰቅላለች፡፡

በሩ ተንኳኳ፡፡ እሌኒ ማብሰያ ክፍል ውስጥ ምግብ እያሰናዳች በመሆኑ መንኳኳቱን አልሠማችም፡፡ ኤልሳ ግን መንኳኳቱን ስለሰማች ፈጥና ወጥታ በሩን ከፈተች፤ ከኤልሳ ጋር ሳምሶንና እንግዳው ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ የውጭውን በር አልፈው ተከታትለው ገቡ፡፡ ሳምሶም በእሌኒ የቤት አያያዝ እየኮራ አባቱን ወደ ሳሎን እንዲገባ ጋበዘው፡፡ የሳምሶም አባትበግቢው ውበት ደስ የሚል ስሜት እየተሰማቸው ወደ ሳሎኑ ሲገቡ ግን ባዩት ነገር ደነገጡ፡፡ የሚያዩት ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ተቸግረው ቆመው ቀሩ፡፡ ኤልሳ ወደ ማብሰያው ክፍል እሌኒን ልትጠራ ሄዳለች፡፡

“አባዬ ቁጭ በል እንጂ! ይኸውልህ የወደፊት ሚስቴ ባለሙያ የቤት አያያዝ የምታውቅ ናት፡፡ አሁን ትተዋወቃላችሁ ፍቅር ፍቅር…” ሳምሶም ተጣራ፤ የሳምሶም አባት አቶ ፍሬው የሳምሶምን እጅ ጨምቀው ይዘው ከእንቅስቃሴ ገተው አስቆሙት፡፡

“ሳምሶም የፍቅረኛህ ስም ማን ነው? እሌኒ ሰውነት እዚያ ላይ የተሰቀለው ፎቶ የማን ነው?”  የእሌኒ እናት! ምነው አባዬ ችግር አለ? አቶ ፍሬው አንገታቸውን ደፉ እንባቸው በአይናቸው ግጥም ብሎ አቀረዘዘ፡፡” ይሄኔ እሌኒ እጇን ተጣጥባ በውበት ላይ ውበት ጨምራ ብቅ አለች፡፡  ሳምሶም በአባቱ ሁኔታ ግራ ቢጋባም እሌኒ ስለመጣች ለማስተዋወቅ ሞከረ፡፡

“አባ ይቺትልህ የኔ የልቤ ላይ ንግስት እሌኒ ያልኩህ፡፡”

አቶ ፍሬው ካቀረቀሩበት ቀና ብለው እሌኒን ተመለከቷት፡፡ በህጻንነቷ ጥለዋት እንደሄዱት አይደለችም፡፡ በጣም ተለውጣለች ለሥራ ከሀረር አዲስ አበባ በተቀየሩበት ወቅት ከትዳራቸው ውጭ ከአከራያቸው ልጅ ጋር በፈጠሩት ግንኙነት ነበር እሌኒ የተፀነሰችው፤ የእሌኒን መጸነስ ሲያውቁ የጀመሩትን ጨዋታ አቋርጠው ትዳራቸው እንዳይናጋ በማሰብ ሥራቸውን ለቀው ወደ ሀረር ተመለሱ፤ ለእሌኒ ግን ባለቤታቸው ሳትሰማ ተቆራጭ ያደርጉ ነበር፡፡ አቶ ፍሬው ቋሚ ስራቸው ሀረር ሆኖ ሳምሶምና ወንድሞቹን በፍቅር አሳድገው ለቁም ነገር አበቁ፡፡ የእሌኒ እናት  ቤተሰቦቿ አዋረድሽን ብለው ለጊዜው ቢያንኳስሷትም ጨክነው አልጣሏትም፡፡ ልጇን እንደ ልጃቸው ተቀበሏት፤ እሷም ከአቶ ፍሬው በሚላክላት ተቆራጭ እየታገዘች ሳትቸገር አሳደገቻት፡፡ ሆኖም ከአምስት አመት በፊት በደረሰባት የመኪና አደጋ ህይወቷ አለፈ፡፡ አቶ ፍሬው የእሌኒን መሞት ሰምቶ ወደአዲስ አበባ ቢመጣም እሌኒን ግን ለማየት አልቻለም ነበር፡፡ እሌኒ ከእናቷ ሞት በኋላ ከአያቶቿ ጋር የኖረችው ለአንድ አመት ብቻ ነበር፡፡ የዩኒቨርሲቲው ውጤት ስለመጣላት ወደ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ መጣች፡፡ ተምራ ተመረቀች፣ እራሷን በራሷ ማስተዳደር ጀመረች፡፡ አያቶቿ በስማቸው እንድትጠራ ከመወለዷ ጀምሮ ጫና በማድረጋቸው የምትጠራው በእናቷ አባት ስም ሆነ፡፡ የእሌኒ እናት በዚህ ቅር አልተሰኘችም፤ አባቷም አቶ ፍሬው ለሥራ ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ አልፎ አልፎ ለማየት ቢፈልጉም በእሌኒ አያቶች እንቢ ባይነት ሊያይዋት አልቻሉም ነበር፡፡ ሆኖም አድራሻዋን በማፈላለግ የሚያስፈልጋትን ሲልኩላት ቆይቷል፡፡ ትምህርት ጨርሳ መመረቋም ሰምተው ተደስተው በስልክ አነጋግረዋታል፡፡  አሁን ባህር ዳር የተገኙት ልጃቸው ሊያገባ መሆኑን ስለገለፀላቸው በእግረ መንድ ልጃቸው እሌኒን እግኝተው፣ በሳምሶም ሠርግ ላይ ታድመው ለመመለስ ነበር፡፡ ሆኖም ሰርጉ የሁለት ልጆቻቸው ጥምረት ሆኖ ድንገት ናላቸውን አዞረው፡፡ ሁለት ልጆቻቸውን ቁጭ አድርጎ ማስተዋወቅ ሲገባቸው ይህን ባለማድረጋቸው ትልቅ ችግር ውስጥ ተዘፈቁ፡፡

አቶ ፍሬው ቀና ሲሉ የተመለከቷት ልጃቸው፣ በጥርጣሬ ተመልክታቸው፤ “አባዬ እንዴ እንዴት እዚህ ልትመጣ ቻልክ?” አለች እሌኒ ግራ በመጋባትና በጥያቄ መንፈስ እየተጠጋቻቸው፡፡

“እሌኒ ልጄ፤ በደንብ ለየሽኝ፡፡ እንዴት ነሽ?”

“ምን አባባ ምን እያልክ ነው?” አለ ሳምሶን ግራ በመጋባት ከመቀመጫው ተፈናጥሮ በመነሳት፡፡ ኤልሳ ለእንግዳው የሚሆን የተሰናዳውን ምግብና መጠጥ ማቀራረብ ብትጀምርም ጆሮዋ ውስጥ ጥልቅ ያለው ነገር ከቆመችበት እንዳትንቀሳቀስ አስሮ ይዟታል፡፡

“ሳምሶም እሌኒ ……እህትህ ናት”

“አላምንም?”

“አዎ የአባትህ ልጅ ናት በአንድ ወቅት ለሥራ አዲስ አበባ በሄድኩበት ጊዜ ያፈራኋት - የአባትህ ልጅ፡፡”

“እንዴ አባባ ምን እያልክ ነው? ለምን አልነገርከኝም?”

“ትዳሬ እንዳይበተን እናንተ ልጆቼ እንዳትጠሉኝ በመፈለጌ ነበር ታሪኬን የሸሸኩት፡፡ ግን ምንም ነገር ተደብቆ አይቀርም፡፡ በስውር የተሰራ በገሃድ በአደባባይ አንድ ቀን ይጋለጣል፡፡” አቶ ፍሬው በሁለት ልጆቹ መሀል ተንበርክኮ “ልጆቼ የጉልበቴ ፍሬዎች እባካችሁ ይቅር በሉኝ የሠራሁት ስህተት ትልቅ ነው፡፡ ለዚህም የሚያበቃኝን ያህል በዚህ ክስተት ተፀጽቻለሁ፡፡ ይቅር በሉኝ እንደገባኝ ሁለታችሁ ለጋብቻ ተሳስባችኋል፡፡ ወንድምና እህት ናችሁና ይህ ጋብቻ መልካም አይደለም፡፡”

“የአባት ፍቅር ሳላገኝ አደግኩ፡፡አሁን ደግሞ በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ያፈቀርኩትን ሰው ልጣ? አላደርገውም፡፡” አለች እሌኒ እውነቱ እየጎመዘዛት፡፡

“ልጄ እባክሽ ይቅር በይኝና ጋብቻውም ይቅር፡፡ ሳሚ ልጄ ይቅር በለኝ?”

“እሌኒ የኔ ፍቅረኛ እህቴ? ቅዠት መሆን አለበት፡፡”

ልጆቼ እመኑኝ በደስታችሁ የምደሰት የጉልበቴ ፍሬ ናቸሁ፡፡ ጋብቻችሁ በወንድምና በእህት መካከል የሚደረግ ነውና መልካም አይደለም፡፡ አባት ያልባረከውም ጋብቻ አይባረክም፡፡ ጥፋተኛነቴን አምኛለሁ ካደጋችሁ በኋላ እንኳን ማስተዋወቅ ነበረብኝ ግን አላደረኩትም፡፡ ስህተቴ ብዙ ስህተቶችን ወልዷል፡፡  የእናንተ ጋብቻ ደግሞ ተጨማሪ ስህተት አይሁን፡፡ ይቅር በሉኝ፡፡ አሁን የእናንተ ይቅርታ ብቻ ከበደሌ እንደሚያነጻኝ አምናለሁ፡፡ ብቻ ይቅር በሉኝ፡፡”

እሌኒ ቀና ብላ በደፈረሰ ስሜት ሳምሶምን አየችው፡፡ በቅፅበት አይን ለዓይን ተጋጩ እሌኒ “ፍቅሬ ስልህ የኖርኩት አንተን ወንድሜን ማመን ከበደኝ እኮ!” አለችና ሳምሶን ላይ ተጠመጠመችበት፡፡ ሳምሶምም እቅፍ አድርጓት እንባውን አፈሰሰ፡፡ ሁለቱም ተንበርክከው የሚማፀኗቸውን አባት እጃቸውን በመስጠት አንስተው አቀፏቸው፡፡



BDU's female students receiving training on the struggle and successes of Ethiopian women in general and the challenges female students faced in the university



House of People's Representatives Human Resource Standing Committee interacting with BDU top management to discuss on teaching-learning, research and community services activities being undertaken by the university




A workshop focusing on BDU's College of Health and Medical Sciences' specialized teaching hospital progress held



የአካል ጉዳተኞች ቀን በዩኒቨርሲቲው ሲከበር አካል ጉዳተኞች የስፖርት ውድድር ሲያደርጉ

**የተማሪ እይታ፡** በዚህ አምድ ስር የሚቀርቡ ፅሁፎች ተማሪዎች ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ሀሳባቸውን፣ እይታቸውንና ፍላጎታቸውን የሚያቀርቡበት ነው!

# Interview with Professor Frank Ashall



**(This interview is conducted through online chat)**

**By Meklit Garedew Gebrewold**
**(meklitgebrewold@gmail.com)**

**"I would advise all students to work hard and to see knowledge, above anything else, as their currency for personal success and for helping them to improve their society and make the world a healthier and happier place!"**



**"As a doctor, though, I prefer the British national health system, which provides free healthcare for all. As a doctor, in the USA I saw too many problems... uninsured patients who cannot afford health care, for example. Many people in the USA have large debts because of medical bills that they can barely afford to pay. I don't believe that someone should suffer severe financial problems because they get sick. But if you are well insured medically in the USA the medical care is excellent."**

**Professor Frank Ashall, an associate professor at Addis Ababa University**

**Meklit**

Hello Professor Frank!

**Professor Frank**

Hello, Meklit!

**Meklit**

Thank you for your willingness for this interview

**Professor Frank**

You are very welcome, Meklit, and it's a pleasure and honor to be such a guest!

**Meklit**

Professor Frank you are now working in Ethiopia. How did you come to Ethiopia? Let us begin with this

**Professor Frank**

Okay, Meklit. Well, I have a background in biochemical research and ran a laboratory in London working on tropical diseases for many years, then I went to the USA and went to medical school there and trained and practiced as a doctor for 14 years.

I went back to England with the intention of joining Voluntary Service Overseas (VSO) to work in a developing country in order to use both my biochemistry and medical experience, skills and knowledge.

I found a place to work, in Zambia hospital system but just after that they told me there was a chance to teach medical biochemistry in Ethiopia and that sounded more interesting so I took that up

**Meklit**

Great! So you came to Ethiopia through VSO

**Professor Frank**

Yes.....for 2 years, but after a year I was offered the chance to be an associate professor of Biochemistry and so I took that post and left VSO

That gave me a chance to teach medical students as well as biochemistry Masters students....I love both Medicine and Biochemistry so that was great

**Meklit**

How do you find working for VSO before and where do you teach?

**Professor Frank**

Working for VSO was wonderful, Meklit.... you meet many different volunteers from different countries working in various areas, from education to health to soil science. You also meet many Ethiopians who work for VSO and the VSO community is dedicated and pleasant to be a member of. I taught at Addis Ababa Medical school as a volunteer and really just continued that after I left VSO to be an associate professor

**Meklit**

It sounds VSO works in Ethiopia widely and has a continual program to work on science and education. So you get to meet many people from different cultural backgrounds which I guess opened a door for you to know more about Ethiopia and how interesting to work in Ethiopia. How did you find teaching at Addis Ababa Medical school?

**Professor Frank**

I have learned so much about Ethiopia and Ethiopians and I have become a great admirer of your beautiful country and the wonderful people of Ethiopia!

Teaching in Addis Ababa University has been also a wonderful experience. I find most of the students I have taught here are very enthusiastic and keen to learn and many have impressed me.

I taught in London University some years ago and have always believed in the value of using our experience, knowledge and skills to teach others

**Meklit**

Great! We will come back to our talk about your work at Addis Ababa Medical school later. Tell us about your family, elementary and high school stay?

**Professor Frank**

Really, I loved my upbringing. I lived in a small England village and though we were relatively poor, education was free and paid for by the British government. I did my undergraduate degree and PhD in Oxford University and that was also paid for by the British government, so I was truly blessed.

I am a great believer in the idea that education should be easily affordable for all those who are able enough to go through it!

Strangely enough, Meklit, when I have visited several small communities in Ethiopia I have noticed some similarities with my own village upbringing. Though our cultures are

Continued on page 10

# Interview with ...

Continued from page 9

quite different, it has confirmed to me that people everywhere have a lot in common also.

**Meklit**

How blessed you are! The British government do pay tuition fee for high school and undergraduate degree for citizens? Yes, Professor Frank I also believe education should be easily affordable for people who could go through it.

**Professor Frank**

Yes, though I think it's changed somewhat since I was a kid, but it's still relatively affordable to go to university and everyone gets free schooling unless they choose to pay privately.

Our children are our future teachers, doctors, nurses, architects, businessmen, politicians and leaders, so we need to give them the best we can!

**Meklit**

Yes our world is full of many different cultures but it is obvious that we do get some common specialties. So you are more than lucky to pass through such a blessing routine!

**Professor Frank**

Yes, and Ethiopia is blessed with such a wonderful diversity of cultures...truly beautiful and impressive.

**Meklit**

We see every family in each village,town,city,country and continent works on getting children the best education access in each level.

Yes, I do give my word that it is her diversity power which attracted you indirectly to Ethiopia!

**Professor Frank**

Well it was a basic belief that we should use our values, experience and education to teach and help others, especially young people, and the belief that we are all citizens of the world

**Meklit**

Hehehe. Yes, Ethiopia has cultural diversity.

**Professor Frank**

Medicine is also a topic that should be based on values that are universal...

that everyone has a right to basic medical care and that Medicine is a noble pursuit that is aimed at helping improve the health of others

As a doctor in the USA I did find that the medical system there was very much a business-oriented system

**Meklit**

The core focus of every medical organization should be helping others get equal medical service so that every citizen of the world has a power which is "health"

**Professor Frank**

Doctors are privileged to have a medical education and I believe strongly in Medicine as a pursuit aimed to provide good health, both preventive and non-preventive, to people. Ethiopia has a very high patient-to-doctor ratio (I believe it's about 35,000 patients per doctor) whereas in the UK and USA it's about one doctor per 400 people.

So, medical students here have a lot to contribute to the health of Ethiopian people.

**Meklit**

Yes Professor Frank, there is a lot to work on reaching people who are in healthcare need especially in Africa. And African medical students have a lot to work on this on the years heading.

**Professor Frank**

I know medical school is tough - I went through it myself - but by students focusing on the noble ideals of Medicine, they can better learn and also focus their goals on the common good of society

**Meklit**

Yes Professor Frank. What do you advise about the focus of most medical students should be?

Here there are many strange things medical students hear about how hard it is to pass through medical studies at their stay at medical school in each level.

**Professor Frank**

The focus should be on enjoying the knowledge they learn...the more they learn, the better doctors they will be. Also, they should try and enjoy medicine in it's own right as an interesting subject. Importantly, though, they should always see that their goals are to help people and eventually, as doctors, to contribute to improving the health of their fellow human beings.

Medical school is not easy anywhere, but if it is approached properly, as a humanitarian and noble pursuit, a privilege, with hard work and positive goals to help others, it is easier to get through!

**Meklit**

Professor Frank, tell us how did you plan to study in the States?

**Professor Frank**

Well, I ran a research laboratory in the UK and moved with my ex-wife to the USA and did biochemistry research there, then I thought it would be wonderful to do a medical degree in the USA to add to my experience of a biochemist. Medicine really has become very biochemically-oriented over the last few decades.

I often teach students that "All diseases are disorders of biochemistry."

**Meklit**

What made you to think and decide to study Biochemistry though?

**Professor Frank**

When I was at high school I wanted to be a medical doctor, but my school chemistry teacher suggested I should study biochemistry, which I loved, so I took his advice.

**Meklit**

I see you are professional in the field you chose to study so far and still working on Biochemistry based issues.

**Professor Frank**

It's wonderful if you love a subject you are learning, and get inspiration from it...it's possible with the right attitude to improve ones love of a subject also!

**Meklit**

What inspired you to study Biochemistry ?

**Professor Frank**

It was the passion for the subject...that living organisms and diseases can be explained at the molecular level

Molecules in living cells are also amazing....I see them as a privilege to learn about because they are as beautiful and awesome as flowers, rivers and trees, but if you don't study biochemistry you never get to "see" them!

**Meklit**

So you are telling us "Biochemistry" is base for every insight we might have about living cells!

Continued on page 14

# Who was the seed?

**Melaku Wale (PhD)**
**Bahir Dar University**

First of all, I need to make one thing clear. I swear I am neither racist nor ethnocentric, have never been obsessed or consumed by irredentism of all its ugly forms. I am simply trying to hunt for facts and knowledge, simple as that.

What is the point? This is a bit of history about the distant past.

Fifteen years ago a friend of mine studied in South Africa for his terminal degree. He found himself there at the aftermath of the downfall of the apartheid regime. There he found a white man who was still in the racist mentality. The white man believed that there is no nation around the globe that is civilized and a black nation at the same time. "Just count and you don't find one", the race concerned person commented. Many such people have the same belief. Even you may find black people who doubt the equality of races as a human being. Human belief is something man-made, artificial, not something natural or biological.

And this happens because of ignorance. Many people either do not know history or they are not interested in history. I am not one of them; I love history. History made today and it will make tomorrow. I myself am the result of history, I believe. Today is the child of yesterday. Nobody can be outside of history. That is the point.

The fact of the matter is that Africa (specifically the Ethiopian region which extended from the Horn of Africa and the Nile Valley to Egypt) gave the world the seed for not only humanity but also the seed for civilization. What was it that happened? It is a known fact that humanity evolved in Africa, the race of which was black. This is not a theory to be contested. It is simply the fact. Egyptians themselves who built pyramids were black.

The one thing most people do not know is not the source of the seed for humanity but the seed for civilization. The origin of humanity is less contested than the origin of civilization. It was not any other race than the black one that has started the first ever civilization, the seed for civilization, as I call it. The civilization that we enjoy today and the one that is still growing started in the Nile Basin namely Ethiopia and its surroundings. The ancient Ethiopians, also known as Nubians, started the very first civilization, which was adopted first by Egyptians and from them by other races, who inhabited the Middle East and the Mediterranean region or Europe.

Yes, there have been other civilizations in other parts of the world such as the Chinese, the Indian and the Mayan to name the most prominent ones. But these other civilizations served their own time and neighborhoods and were not inherited by the contemporary civilization. Their contributions are not clearly seen in today's civilized culture. No question, European (Western) civilization leads today's world, though that does not give Europe the liberty to be the originator of civilization. Europeans simply improved it. If at all some of the contributions of other old civilizations (such as the Chinese, Indian or the Mayan) were evident, those were incorporated thousands of years afterwards. They only added to what was there already. Such contributions are still ongoing even today. Contributions always happen and they are not limited to the above groups only. Every human society contributes a bit to today's mainstream civilization. The very first ones who started the engine were the ones from the Nile Valley.

At the time Stone Age Europeans were living in caves and gathered fruits and roots, and when most Asians were simply pastoralists, Ethiopians lived in civilized cities. They lived in houses built out of clay bricks of the same quality as bricks today. They wrote narrations in text and symbols. They inscribed their physical complexion on stone. They made statues of their kings and nobles. All these were done 3 thousand to 4 thousand years before the birth of Christ. That was prehistory when Europe was at the Stone Age living in caves.

Nubians (Ethiopians) ruled the entire Nile Basin and nearby territories including Egypt. They built pyramids which were technologies that were later adopted by Egyptians themselves. The Ethiopians domesticated animals and crops. They were sophisticated in civil engineering and also in military power of their time. Evidences for these are archaeological remains that still exist today. Ethiopians transferred all these technologies (pyramids, domesticated animals and crops, civil engineering, military and religion) to the nearby subjects. That time the Arabs, who resided nearby, were herders, while Europeans were collector-gatherers.

Gradually Egyptians became independent from Ethiopia while adopting the civilization that came from the south. The original inhabitants of Egypt who started the dynasties (pharaohs and their people) were black; look at their statues, you will see black physical complexion. Arabs and other races came later to Egypt, specifically after Mohammed and his followers became prominent in the region. Slowly Egypto-Ethiopian civilization was taken over by the nearby Europeans such as the Greeks and the Romans, who were neighbors of Egypt and the Nile Valley. The Romans advanced it further west to the fringes of the continental Europe and beyond. Then there was no return or decline. Civilization was set in motion by Ethiopians and once it was adopted by Europe from Egypt, it maintained a steady growth. Europeans knew that civilization was possible, was good and it added spice to the way of life. For example, the British liked the Roman engineered cobblestone roads (which were virtually unknown in Britain before Romans subdued them) and the British maintained the tradition ever since. The tempo and variety of civilization was intensified by Europeans, the seed of which has come from Ethiopia, nurtured in Egypt. Ethiopia, on the other hand, neither sustained nor developed its creation. It was kind of decay. Whether it was because of internal or external factors is unclear. Nevertheless that does not mean that it was a one- time phenomenon. They have used that civilization for longer period than the whole of the modern (European) civilization combined. Historical evidence shows that they have been improving it to their own time as time passed by.

Then came a time when Europeans returned the old civilization back to Africa and in a different form and variety. So the old civilization had to be replaced by a better, modern one. In other words, Europeans made it universal at around the turn of the 2nd millennium. That happened more than about 3 thousand years after seeds for civilization were set in motion. Had there been no humans in the Nile Valley, there would have been no seed for civilization and Europeans would have stayed in the Stone-age until the end of time. Today's sophistication would have not existed. Space exploration would have been impossible. Atomic exploration would have been unthinkable.

In fact, Europeans are never hesitant to acknowledge the origin of all civilization being in the Middle East.

Now, one question remains unanswered. It is impossible to claim that other civilizations around the world that were comparable to the one in the Nile valley did also serve as seeds themselves. Why not? Why can't we say these ones also served as seed for civilization? The answer is that we cannot take these ones as seeds for today's civilization because they all were disconnected and physically separated from Europe, an area where the modern civilization was nurtured and donated back to the world. The distance that separated them was long at least

**continued on page 12**

## ቁጭ ብለን የሰቀልነውን ...

ከገጽ 6 የዞረ

ስብዕና ግን ሊያዳብርላቸው እንደሚችል አልጠራጠርም፡፡ ማዕረጉም ይነስ ይብዛ እንጂ ከቶስ ከወታደር ቤት በላይ ወታደራዊ ዝንባሌ እና ማንነት ከየት ሊዳብር ኖሯል?

### የሥራ ህይወት

ሐብቴ ምኒሊክ ቤተ-መንግስት ከመጡ በኋላ ሥራቸውን ‹‹ሀ›› ብለው የጀመሩት ለባልደረሱ (የፈረስ ቤቱ ሃላፊ) ረዳት በመሆን አዳዲስ ፈረሶችን በመሞከር፣ በመቀለብና ንጽህናቸውን በመጠበቅ ነበር፡፡ ከሁለት አመት በኋላም የእልፍኝ አሽከሮች አለቃ በመሆን ተሾሙ፡፡ አንኮበር ጊዮርጊስ ለ‹‹ስኮላርሽፕ›› ተልከው ፊደልና ንባብ ከተማሩ በኋላ ተመልሰው አሁንም በቤተ-መንግስት ውስጥ በባለሟልነት ተመድበው ስራቸውን ቀጠሉ፡፡ ለተመደቡበት ሥራ የሚሠጡት አገልግሎት እና የሚታይባቸው የኃላፊነት ስሜት አለቆቻቸውን በሙሉ የሚያስደንቅ በመሆኑ አፄው ከጭንጫ አሽከርነት አንስተው ለልጃቸው አስፋው ወሰን ሰጥተውት የነበረውን የበቾን ግዛት በምስለኔነት እንዲያስተዳድሩ ሾሟቸው፡፡ እዚያም ህዝቡ ስላመሰገናቸው ወሊሶና አመያ አውራጃን ገዥ ሆነው ተሾሙ፡፡ እዚህ መግባታቸው ነበር ታዲያ ሁለተኛው የእድል በራቸው ወለል ብሎ እንዲከፈትላቸው ያደረገው፡፡ እንዴት አላችሁ? እዚህ በመሾማቸው የወሊሶና አመያ ሠራዊትን ይዘው ወደ አደዋ እንዲዘምቱ እድል ፈጠረ፡፡ በአደዋ ጦርነት በየትኛው ግንባር እንደተዋጉና ጀግንነታቸውን በምን አኳኋን እንዳስመሰከሩ በዝርዝር ባይታወቅም በጦርነቱ ወቅት ሁለት ያበረከቷቸው ወሳኝ ሃሳቦች ግን በምኒሊክ አይን ለትልቅ ቦታ እንዲታጩ መሠረት እንደጣለ ይታሰባል፡፡

ከላይ በጠቀስኩት እንደ ሌተና ኮሎኔል አበበ ወ/ተንሳይ መጽሀፍ ከሆነ በ1888 ዓ.ም ጣሊያኖች ኢትዮጵያዊያን በጦርነት ሲያይሉባቸው እርቅ ይጠይቃሉ፡፡ አብዛኞቹ መሳፍንትና መኳንንቶች እርቁን ሲቀበሉ ሐብቴ፣ ራስ አሉላ አባነጋ እና እቴጌ ጣይቱ ግን ውድቅ ያደርጉታል፡፡ እርቁ የቀረበው ‹‹ጣሊያን ለጦርነቱ ሌላ ዘዴና ዝግጅት ለማድረግና አገር ለመውሰድ አስቦ ነው›› በሚል አመክንዮ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ከብዙዎቹ መኳንንት እና መሳፍንት ይልቅ የእነ ሐብቴ ሀሳብ በንጉሱ ፊት ተቀባይነት አግኝቶ የአድዋ ጦርነት በኢትዮጵያ ድል አድራጊነት ተደመደመ፡፡

ሁለተኛው ደግሞ በዚሁ ጦርነት ላይ ወሳኙ የየካቲት 23 ውጊያ ከመፈንዳቱ በፊት ሐብቴ ለበላዮቻቸው የሚከተለውን ሐሳብ እንዳቀረቡ ዘውዴ ረታ ጠቅሰዋል፣ ‹‹ለጠላታችን የፊት ለፊቱን መንገድ ብንለቅለትና የሸሸነው አስመስለን በጀርባው ዞረን ብንከበውና ብንወጋው ድሉን በቶሎ እናገኛለን፡፡›› በዚህም <<ስትራቴጅክ>> ሃሳብ ምኒሊክ ተደምመው ከአጠገባቸው እንዲሆን የጦራቸውን ዋና አበጋዝ ፊታውራሪ ገበያሁ ገቦን (አባ ጎራው) አዘዙ፡፡

አባ ጎራው ሐብቴን አምጥቶ ካስቀመጠ በኋላ በጦርነቱ ሰማዕት ሆነ፡፡ ጦርነቱ ከተጠናቀቀና 9 ወራት ካለፉ በኋላ አፄው የአገሪቱን አስተዳደራዊ ስርዓት ለማዘመን በመሠረቱት የ12 ሚኒስተር መስሪያ ቤቶች ሹመት ላይ ሐብቴ አባ ጎራውን ተክተው ከሹመቶች ሁሉ ትልቅ የሆነውን የጦር ሚኒስተርነቱን ቦታ ተሰየሙበት፡፡ አገር ታዲያ ጉድ አለ፤ ደማቆቹ እነ ባልቻ አባ ሰፎ (ልክ እንደ ሐብቴ የራስ ጎበና ምርኮኛ የነበሩ) እና ሊቀመኳስ አባተ እያሉ ደብዛዛው ሐብቴ ሲሾሙ፡፡ በዚህ መሠረት ከባልደራስ ረዳትነት እና የጭንጫ አሽከርነት የተነሱት ሐብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ ተምዘግዝገው በአጭር ጊዜ ውስጥ ‹‹ፊታውራሪ›› የሚል መዓረግ ተሠጧቸው ምኒሊክ ለማንም ፈቅደው በማያውቋት በቅሏቸው ‹‹ቡሊ›› ሰግረው የራስ ወርቅ ታስሮላቸው የስልጣን ሹመታቸውን ተቀበሉ፡፡ ብዙዎቹ የዘመኑ ሰዎች ደግሞ በጉብዝናቸው ስለሚወዷቸው ‹‹ጌታ›› የሚል ምዕላድ ቀጥለውላቸው ‹‹ጌታ ፊታውራሪ›› ተብለው መጠራት ያዙ፡፡ ኋላ ላይም ስልጣናቸው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢነትን ሲያካትት የጠቅላይ ሚኒስትርነትን ሚና የሚያጫውት ደረጃ ላይ ደረሰ፡፡ የስኬት ጉዟቸውን ሳየው ልክ ከተለማማጅ የፋብሪካ ሰራተኛነት (Apprentice) ተነስቶ እስከ ግዙፉ ኢንዱስትሪ መሪነት (Chief Engineer or General Manager) የደረሰውን ኃላም በስራ አመራር ጥናት መስክ የመጀመሪያውን መፅሐፍ በማሳተም (The Principles of Scientific Management) የዘርፉ አባት ተብሎ የሚጠራውን ፍሪደሪክ ዊንስሎ ታይለርን መሰለኝ፡፡

በአጠቃላይ ሐብቴ የጦር ሚኒስትር ከሆኑ በኋላ በአገሪቱ የጦር ጉዳይ ብቻ ሳይወሰኑ ሁለንተናዊ በሆነው ፖለቲካዊና ማህበራዊ ህይወት ላይ ቀጥተኛና ከማንኛውም የዘመኑ ሚኒስትር የበለጠ አሻራቸውን ማሳረፍ ቻሉ፡፡ የሐብቴ ፖለቲካዊ ስልት ረጋ ብሎ እና ድምጽን አጥፍቶ ከኋላ በመሆን የለውጡን (ነውጡን) ‹‹ሴንፎኔት›› ‹‹ኮንዳክት›› ማድረግ እንጂ እንደ ዘመኑ የዋህ መሳፍንትና መኳንንት ‹‹ኧረ ጎራው›› በማለት አቧራ እያስነሱ በጭሱ ታፍኖ መሞት አልነበረም፡፡ በዚህም አጨዋወታቸው ተጠቀመው ካስቆጠሯቸው የፖለቲካ ግቦች ውስጥ ሁለቱ በአገሪቱ ፖለቲካ ውስጥ እጅግ ወሳኝ ቦታ የያዙ ናቸው፡-

1. ምኒሊክ ታመው በነበሩትና አስተዳደራቸውን ለልጅ ኢያሱ ሞግዚት ለራስ ቢትወደድ ተሰማ ናደው (አባ ቀማው) ባስተላለፉበት ወቅት የሞግዚቱን አስተዳደር በማዳከም እቴጌ ጣይቱ ስልጣኑን በራሳቸው ሰዎች መሙላት ሲጀምሩ እቴጌዋ ከፖለቲካ አለም ተገለው ባላቸውን በማስተመም ብቻ እንዲወሰኑ፤ ምኒሊክም ከሞቱ በኋላ ከፖለቲካ ጨዋታ ውጭ ሆነው ኑሯቸውን በምንኩስና በእንጦጦ ማሪያም ቤተክርስቲያን ተገድበው እንዲገፉ ያስገደደውን ፖለቲካዊ ምስጥር (Conspiracy) የሸረቡትና የመሩት ሐብቴ ነበሩ፡፡ ሆኖም ከስልጣን የመገለሉን ዜና ለእቴጌዋ ያረዱትና የተረጎሙት ግን ራስ ቢትወደድ ነበሩ፡፡

2. አቤቶ ኢያሱን (አባ ጤናን) በመገልበጥ ተፈሪ መኮንን (የኋለኛም ቀደማዊ ሐይለ ሥላሴ ወይም አባ ጠቅል) ወደ ስልጣን ለማምጣት የተሠራውን ደባም በተመሳሳይ መልኩ ከጀርባው ሆነው የመሩትና በቁጥርም ሆነ በብቃት አቻ የማይገኝለትን የልጃቸውን አልጋ ለማስከበር 60,000 ጦር ከወሎ ይዘው ወደ ሸዋ የዘመቱትን ንጉሰ ጺዮን ራስ ሚካኤልን (አባ ሻንቆን) አንዴ እርቅ ፈላጊ መስሎ በመቅረብ (ልክ ጣሊያኖች ኢትዮጵያ ላይ እንደሞከሩት)፣ እንዲሁም የሀሰት ፕሮፖጋንዳዎች በመልቀቅ (ንጉስ ሚካኤል ሳይማረኩ ተማርከዋል በማለት)፤ በሰገሌው ጦርነት ድሉን በእጃቸው አስገብተዋል፡፡ የሰገሌው ጦርነት ኢትዮጵያዊው ኢትዮጵያዊ ወንድሙን ደም በማፍሰስ የተገኘ ድል ስለሆነ የሚያኩራራ ባይሆንም የሐብቴን ወታደራዊ ስልት እውቀት ግን እንዳስመሰከረ መርሳኤ ኃዘን ወልደ ቂርቆስ ‹‹የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ›› በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ አስገንዝበዋል፡፡

ቀልድ አዘል ጥበባዊ ውሳኔዎቻቸውን የሚያስቃኘውን የሕይወታቸውን ክፍል በሚቀጥለው እትም ይጠብቁ.....

(በዚህ ፅሁፍ ላይ ሙያዊ አስተያየታቸውን በመስጠት ፅሁፉን ላዳበሩልን የታሪክ ምሁር ዶ/ር ፋንታሁን አየለ የዝግጅት ክፍሉ ላቅ ያለ ምስጋናውን ያቀርባል፡፡)

## ፍቅር.. ዳርም የለሽ...

ከገጽ 13 የዞረ

ስለተገኘ ነው፡፡ ባለመኖር ውስጥ ያበበ አበባ፣ ያማረ ፀዳል መስሎ የኖረ በተዘጋ ልብ ውስጥ ሳያንኳኳ የዘለቀ፣ ለወየበ ላደፈ ሀሊና ትንሳኤ ስለሆነ.... ፍቅር ዝም ነው! ፍቅር ልሳን እንጂ ቋንቋ አይደለም፡፡ ፍቅር ሰብዓዊ ነፃነት እንጂ ስጋዊ ግዴታ አይደለም፡፡ ፀሐይዬ.... እኔ ላንቺ መኖር ተቀንሼ... ላንቺ እስትንፋሴን ተለጉሜ... የከፈልኩትን የመድደድን ክብር፣ ስለምን ለመኖርሽ ዋጋ የከፈለልሽን የታመመ ልቤን ወዲያ ፈንግለሽ ጣልሽው... እንደ አሮጌ ጫማ... እንደማስቲካ አኝክሽኝ፣ አላምጠሽ ተፋሺኝ... እሁ.... ጥቅም.... አንድ ህሊና የሚፈልገውን ለማግኘት ዳክሮ ... ዳክሮ እየባጠጠ ከሄደ በኋላ... ሰባት ጊዜ ወድቆ... ሰባት ጊዜ ሞቶ የሚያገኙት በመጨረሻም ለመሞት ትንሳኤ የሚሆን አንድ አላማ ነው አላማ ደግሞ ብልሀት ነው... ለብልሀት ደግሞ ማፍቀር... መፈቀር... ፍቅር ውታፍም፡ ስሜትም፣ ድህነትም ነው፡፡ ፀሐይዬ... በውታፍ ስም ልፃፍልሽ.. ፍቅርን ውታፍ ብዬ በገለፅኩበት.. ያለመወሰን ወሰኜ ልቀኝልሽ.. ባለሽበት አለም እኔም ባለሁበት አለም እዛው ከትመን እዛው እንስራ... እስካፈቅርሽ.. አላፈቀርኩሽም.. እስክወድሽ.. አልወደድኩሽም.. በዘቀጥሽበትና አንኳር ከሆንሽበት አለም ውስጥ እዛው ፍኪ... እዛው ብሪ.. ካጠቆርሺው ንጪ... ያለምንም... ያለማንም... ላለማንም ያለምንም ኑሪ... አፍቅሪኝ... አለበለዚያ ማፍቀሬ ባዶ ነው! ምክንያቱም ፍቅር መዋሀድ ነውና... አፍቅረሽ ስትመጪ... አፍቅሬሽ እመጣለሁ.. ያኔ የማይደረመስ ፍቅር እንሰራለን፡፡

**ያንቺው አፍቃሪ፡- ደረሰ አማረ**

# Who was the seed? ...

**Continued from page 11**

for their time. The Mayans, Indians, and Chinese did not have contact at that time. These civilizations were discovered as a result of the already functioning Western civilization itself. There is no history of connection between Western civilization and them as the one we see with Africa and or Egypt and the Middle East. When it comes to Africa, geographic proximity played the role. The Civilization started in Nile Basin, just a neighbor of Europe, and steadily went on to expand in the Middle East and Europe. Europe was the one and only destination that gave its final shape.

Europeans are credited for advancing it so high that it would never fail a second time, as the one we saw in the Nile Valley. Mind you in Africa it simply was made clear that civilization was possible, not maintain the pace. It just transferred the seed and itself went back to its old ways, almost. Europe gave it the modern shape and ensured universal acceptance.

But ancient Ethiopians need also to be credited for starting the civilization though for some reason they did not maintain the momentum **right on the spot**.

Countless archaeological remains support the evidence reported here.

So the South African guy may have to think twice before hastily concluding about the place of the black race in history and civilization of humanity.

# ፍቅር.. ዳርም የለሽ

በዛሬው ቆይታዬ የማይጠገብ የማይሰለች ጉዳይ ላውጋችሁ? አንባቢያን «ወገኛ» ብላችሁ ቁም ነገሬን ብታስቀጥሉኝ ምነኛ ደስ ባለኝ! ብቻ የፍቅርን ጥግ ለማወቅ የዳከርኩበት ጎዳና እንደ አድማስ እየረዘመ አቅሌን አስቶኝ ደክሞኛል፡፡

ወደ ዶርሜ ገብቼ በጉዞ የደከሙትን እግሮቼን «በርከክ በሉ» ብላቸው በርከክ ቢሉ እኔ ወንድማችሁ ለጥ፣ መተኛት ነዋ! ድምፄን አጥፍቼ ለሽ! ... በእንቅልፍ ልቤ የነገውን ቀጠሮ እያሰብኩ...... አይነጋ የለ ነጋ! ቀን ቀንን ተካ ማለት ነው? በጥዋት ተነስቼ የማለዳዋን የባሕር ዳር ፀሐይ እየሞቀኩኝ ነው፡፡ ለነገሩ መሞቅ አይባልም መቃጠል... ነው እንጂ... ይገርማችኋል የፔዳ ግቢ ፀሐይ ገና ጎህ ከመቀደዱ ፀሐይዋ ከነልጅ ልጆቿ የወጣች ያህል ይሰማኛል፡፡ ብቻ ምን አለፋችሁ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለፀሐይ ቅርብ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ው...ይ! ...ወይ! በሞትኩት! እኔን ሞት ይርሳኝ... ሌላ ምን እላለሁ... እራሴን ሳላስተዋውቃችሁ! ... ለማንኛውም ስሜ ደረሰ አማረ ይባላል፡፡ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጆርናሊዝምና ኮሙዩኒኬሽን ትምህርት ክፍል የአንደኛ ዓመት ተማሪ ነኝ፡፡ አሁን በጥቂቱም ቢሆን ሳታውቁኝ አልቀራችሁም ... ወደ ቀደመው ነገራችን እንመለስ ... በዛሬው እቅዴ መሰረት... የመጀመሪያው የግቢያችን የካፌ በር ሳይከረቸም ቁርሴን መብላት ... ይገርማል! ይሄም እቅድ መሆኑ ነው? ግን እኮ የት አባቱ ዛሬ ባይበላስ? «ምግብ ባሳደገ ደመኛ ነው እንዴ» ... ዛሬ ወደድኩም ጠላሁም ቁርስ ተዘሏል ... ያው በእናቴም፣ በአባቴም ሀበሻ አይደለሁ?! የምሳዬን እግዜር ያውቃል፡፡ ዩኒቨርሲቲ በገባሁ በወሬ ያወቅኳት ዳርም የለሽ የተባለች ጉብል መልከ መልካም ኮረዳ አለች፡፡ እግዜር ሁሉን አሟልቶ ሰጥቷታል ብል አያስገርምም፡፡ የጣቷን ጥፍር አይታችኋል?! ለነገሩ የት ታዩታላችሁ አታዩትም፡፡ አፍንጫ፣ ቁመና፣ ቅንድቧና የሚገርመው አይኗ፣ ፀጉሯ፣ ከናፍሯ... ኧረ ምኑ ቅጡ... ፈጣሪ ሁሉን አሟልቶ ሰጥቷታል፡፡ ብቻ ምን አለፋችሁ ቆንጆ ናት፡፡ ፀባይዋን ግን እንደምፈተንበት አውቃለሁ፡፡ መቀራረባችን የተፈጠረው ሁለት የተለያዩ ዋልታዎች የመፈላለጋቸውን ያህል.... ምን እንደነካኝ አላውቅም ተጣበኩባት፤ ወደድኳት ብዬ ብላችሁ ምን ገዶኝ?! የእኔ እንድትሆን ከመጓጓቴ የተነሳ ጠየቅኳት፡፡ የሆድ የሆዴን ብነግራት የሴት ልጅ ውበቷ ኩራቷ ይመስል ጥቂት ተጀነነች፡፡ ለካስ በፊት ፍቅርን ታውቀው ኖሯል! ፍርሀት ፍርሀት አላት፡፡ ብዙም ሳታመነታ እሺታዋን ገለፀችልኝ በጊዜው እንደ እኔ ደስተኛ ያለም አይመስለኝም እኔጃ? አላውቅም የሆነ ስሜት ሊያምሰኝ ይሁን ሊያነደኝ እንጃ ይቆሰቁሰኝ ጀመር፡፡ ብቻዬን ማንም በሌለበት ፍንድቅ ብዬ ዋልኩኝ ብል እንዳያስገርማችሁ፡፡ ለጓደኛዬ የተሰማኝን ስሜት ባማክረው «Internal Feeling» ነው ብሎኛል ቁጭ አለ፡፡ አትፍረዱበት የእንግሊዘኛ ተማሪ ስለሆነ ነው፡፡

ዳርም የለሽ ልክ እንደ ስሟ ዳርም ያላት አይመስለኝም ነበር፡፡ ዛሬ ግን ዳር ብቻ ሳይሆን፣ ጥግ ብቻ ሳይሆን፣ ጠርዝም እንዳላት ያወኩት የተጣላን ለታ ነው፡፡ ይኸው ከተጣላን ሁለት ሳምንት አልፎናል፡፡ የተጣላንበትን ምክንያት አልነግራችሁም! ቅጥል! በሉ! «ማን በማን ሽንፈት ይስቃል?»፡፡

ለማንኛውም... በጣም ስላስከፋችኝ ይህን ደብዳቤ ልፅፍላት ወሰንኩኝ በሉ እንግዲህ ስሜቴን ተጋሩት.. ምን ያህል ጨካኝ፣ አረመኔ፣ የፍቅርን ስም የምታበላሽ መሆኗን ተረዱ፡፡ ወይ እኔን ወይ እርሷን ውቀሱ፡፡ ወደ ቀድሞ ቤቷ እንድትመለስ ዘግታው የሄደችውን የልቤን መቃን ዳግም ከፍታ ትገባ ዘንድ ምኞቴ ነው፡፡ በይ እንግዲህ ከሰማሽኝ ካዳመጥሺኝ... በብዕሬ ቀለሜን እያነጠብኩ ልፃፍልሽ

እህ... አየ አንቺ እኔን በከርታታው እና ዘወትር በከበበ ሀዘን ከማይፀዳው ልብሽ እኔን አንድ አልፀና ብሎ ሌላን በሚሻው እና በሚዋትት ስጋሽ... እኔን ሳይሆን... ሌላን በከጀለው... ለጥቅም እንጂ ለፍቅር ኖሮ በማያውቀው የወየበ ህሊናሽ... አስረሺኝ ታስሬ፣ ነክሰሺኝ.. ቆስዬ፣ አፍቅሬሽ.. ተፈቅረሽ.. አንቺም በወዲያኛው እኔም በወዲህኛው አለም ዘቅጠናል፡፡ ልንንሳፈፍ የማንችል፣ ልናይ እንጂ ልንታይ የማንችል የዘቀጠ አተላ ሆነናል፡፡

የሰው ልጅ ተፈጥሮ ሲገርመኝ! በፍጥረት ሀገር እየኖረ እራሱ ፍጡር መሆኑን እያወቀ እንደ እንቧይ ካብ እራሱን እየካበ፣ እንደ ከፍታ ማማ ራሱን እያዘነጠ መስሎት... በድንጋይ ካብ ቤት ውስጥ እራሱን እና ህሊናውን እንዲሁም አስተሳሰቡን ከመሬት በታች ቀብሮ... ስጋውን እና ውበትን ለጥቅም ያስገዛል፡፡ ግን... እኔም... አንቺም.... ፍቅሬም... ንቀትሽም... ለንባብ እንጂ ለፅሁፍ ያልሆነ.. የሚነበብ እንጂ ያልተፃፈ፣ የተሻረ እንጂ ያልተመሰረተ.. ልክ እንደተጣለ የእንግዴ ልጅ እየተላወሰ አለ፡፡ ያኔ ነው! በቃልሽ ቃል ታጥሬ፣ በነፍስሽ ህይወት ሆኜ... በእግሮችሽ እየዳሁ ሰው ለመሆን.. ያፈቀረ ሰው ቆሻሻ ነፃነት ነው! ፍቅር ለእኔ ለአይን የሞላ... ለህሊናዬ የከበደ... በእውነት የተዘራ... በተዘራው ድግምት የሰውን ልጅ አያከሳም አያደልብም አለ፡፡ በቃ! ምንም የለም ባዶ ነው! አለም በፍቅር ተፈጥራ ፍቅር አልባ ሆናለች! ሰው በፍቅር ድኖ የፍቅርን ስም የሚያበላሽ ባለጌ ሆኖአል፡፡ ያኔ.. ያ..ኔ.. ትናንት... ከካቻምናው ግርግም ደመና በከበበው ጉሙ እፍን ጥቅጥቅ ባለበት ሰማይ.. ሰማይ የምታክል ትንሽ መሳይ ትልቅ.. ግን የትልቅ ጉላንጆ... ፀሐይ መሳይ ውበት... ካንቺ ወደ እኔ... ባንቺ ለእኔ ከአምላክ ደረሰኝ፡፡ ፀሐይዬ... .. ያየውሽን እና ያየውበትን ቀን አረሳም... እንዳይጠፋ አድርጌ ደረቴን ሰርስሬ ልቤ ላይ አንግሼዋለሁ..... ስለ ምንም ነገር አፈቀርኩሽ! ምክንያቱም ፍቅር፣ ፍቅር የሆነው... በባዶ

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

# የ ግ ጥ ም ጥ ግ

## እርሱ ነው ሠው

እውነትን የሚወድ ሀሰት የሚጠላ፣
እንደራሱ አድርጐ የሚያስብ ለሌላ፡፡

ተንኮል ምቀኝነት እንዲሁም ሀሜት፣

ከልቡ የሌለ ጥል አድመኝነት፡፡

ሁሌም ቅን አሳቢ ለወገን መከታ፣

ራሱን የቻለ ለወገን አለኝታ፡፡

አንገቱን የሚሠጥ ሁሌም ስለ
እውነት፣

ሁሉን በእኩል የሚያይ እርሱ ነው
ሠው ማለት፡፡

ለራስ ጥቅም ብሎ እውነትን ያልሸጠ፣

በሰዎች ገንዘብ ላይ ያልተሽቆጠቆጠ፣

የጓደኛን ሀዘን እንደሱ አያዘነ

የጓደኛው ደስታ ደስታው የሆነ

በዋዛ ፈዛዛ ጊዜን ያላጠፋ

እርሱ ነው ሠው ማለት ይታወቅ
በይፋ፡፡

ትህትና ልምዱ አክብሮት መለያው፣

እንደ እራሱ አድርጐ የሚያስብ
ለሌላው፣

ትእቢትን የናቀ ተንኮልን የጣላ፣

ቅን አሳቢ ለሰው ያልሆነ ተላላ፡፡

"ሰው ማለት እርሱ ነው" ተብሎ
የተለየ፣

ከመጥፎ ሥራዎች ራሱን የለየ፣

ሁሌም የሚያወራ ተመርኩዞ
በእውነት፣

ሰዎች ልንገራችሁ እርሱ ነው ሰው
ማለት፡፡

ችግር ሲደርስበት ተስፋ ያልቆረጠ፣

እስከ መጨረሻው በትጋት የሮጠ፡፡

የድል፣ የክብር አክሊል የተዘጋጀለት፣

ልብ ብላችሁ እዩት እርሱ ነው ሰው
ማለት፡፡

ሰዎች ሲበድሉት ይቅር ባይ መልካም
ሠው፣

ማስተማር የሚችል ሠው ማለት
እርሱ ነው፡፡

ሀይል የፈጣሪ መሆኑን ያወቀ፣

ድሃ ደካማውን ከእርሱ ያላራቀ፡፡

ለሰዎች አሳቢ ያቅሙን የሚረዳ፣

ለእውነት የሚሞት ጓደኛ 'ማይከዳ፡፡

ለራስ ጥቅም ብሎ ሌላን የማይጎዳ፣

ቅን አሳቢ ለሰው ያልሆነ መሠሪ፣

ስለ ሀገር ፍቅር ስለወገን ፍቅር ሁሌ
ተቆርቋሪ፡፡

ተስማምቶ የሚኖር ከዘመድ አዝማድ፣

"አሉ" ብሎ ማውራት ፈፅሞ
'ማይወድ፣፣

ከአልባሌ ስፍራ ራሱን ያራቀ፣

ከመጥፎ ሥራዎች ያልተደባለቀ፡፡

እርሱ ነው ሰው ማለት ለአገር አሳቢ፣

ሁሌም ለሰው ልጅ ሟች ወገኑን
ሰብሳቢ ፡፡

ሰርክአዲስ ሐጐስ

ሕ/ጤ/ሣ/ ኮሌጅ ቢሮ እና መዝናኛ
ጠ.አገልግሎት

## ወንድ አሏት ያችን ሴት

ሴት ጀግና ሳትጠፋ ከጥንት ታሪካችን፣

በስህተት ተቃኝቶ ስመ-ውዳሴያችን፡፡

የንግስት ህንደኬን& የንግስተ ሳባን

ጀግንነት ረስተው፣

የጣይቱን ገድል አድዋን ዘንግተው፡፡

መማር ሲገባቸው ከጥንታዊ እናቶች፣

ጀግና እንደነበሩ በሁሉም ዘርፍ ሴቶች፡፡

የዘመኑን እንስት ተገደው ሲያደንቁ፣

በየስራ መስኩ ጉብዝናዋን ሲያውቁ፡፡

ተግባሯ ቢያስደስት የሰራችው ስራ፣

ጎላ ብሎ ሲታይ ወገኗን ሲያኮራ፣

በሳይንስ ብትልቅ ተግታ ተመራምራ፣

በፖለቲካው ዘርፍ ወንዶችን ብትመራ፡፡

ስሟን ከድርጊቷ መስጠት ተስኗቸው፣

ወንድ አምላኪ ሆነው ወግ-ልማድ
አስሯቸው፡፡

ወንድ አሏት ያችን ሴት ድል አድርጋ
ስትገባ፣

ጀግና ሴት በማለት ማሞገስ ሲገባ፡፡

ጅዲ. ድናድ

ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ

# Interview with ...

Continued from page 10

**Professor Frank**

Well it helps us to understand cells and diseases at the molecular levelbut there are still the "larger" issues to understand such as muscles, the heart, liver, kidney and brain, as so forth.....we have to learn different levels to understand Medicine, but biochemistry gets it to the molecular level

**Meklit**

Do you think people who are involved in Medical studies do give emphasis on this? I think this help us get to study further on different health ambiguities which still need a solution and cure.

**Professor Frank**

Well medical students should focus on everything they are taught, but they should also pay attention to Biochemistry because it helps them to understand diseases better and if a doctor is well versed in biochemistry it helps them be a better doctor or researcher if they choose that avenue.

**Meklit**

How was your stay in United States?

**Professor Frank**

My two daughters were brought up there, so from a personal point of view it was wonderful. I love the national parks in the USA also- there are so many amazing places to see there. People often think that the USA is all about big cities and skyscrapers, but there is a tremendous amount of natural beauty there also.

As a doctor, though< I prefer the British national health system, which provides free healthcare for all.

As a doctor I in the USA I saw too many problems... uninsured patients who cannot afford health care, for example. Many people in the USA have large debts because of medical bills that they can barely afford to pay. I don't believe that someone should suffer severe financial problems because they get sick.

But if you are well insured medically in the USA the medical care is excellent.

**Meklit**

You have daughters? They must be proud to have a father like you! Did you move to Ethiopia with them? How was moving to United States with a family? Does the British health system still provide free service?

**Professor Frank**

The British health system is available essentially free to everyone, yes, though there are private insurance companies if someone wants to pay for it. I never came across anyone who suffered financial devastation from being unable to afford medical care in the UK.

My daughters are grown up and still live in the USA. One is at University there and the other is doing biochemical research

Even moving to the USA was a little bit of a culture shock, because there are some differences between US culture and British culture!

Strangely enough, I found it easier to move from the UK to Ethiopia!

**Meklit**

So you have a seed in your daughter growing! You must work hard to help them get in to the right line of life where they are capable of to contribute in the Biochemistry root.

**Professor Frank**

Hahaha, well, Meklit, we must let our kids do their own thing, but guide them and inspire them as much as possible.

**Meklit**

Hahaha,okay. I think I have forgotten to ask you about the important part when you pass through these all. Would you tell us about your wife Professor Frank?

**Professor Frank**

My ex-wife works as a professor of biochemistry in New York...she runs a large research laboratory working on Alzheimer's disease

**Meklit**

Oh that is great! So you had "a power house of Biochemistry"! I personally know that you do work on Tobacco. Would you tell us about your work on Tobacco?

**Professor Frank**

I have, for many years, been a campaigner for a world free of tobacco-related diseases. As a child in the Uk I saw many people die from these diseases, such as heart disease and lung cancer. As doctor in the USA I saw many patients also suffer from the bad health effects of smoking.

Ethiopia has one of the five lowest smoking rates in the world, which is something to be proud of. But smoking rates are going up in African countries, so it's important for medical students, nurses, doctors and other health workers to educate their patients not to smoke (or to quit) and to educate children about the dangers of smoking....that way Ethiopia can maintain its low smoking rate and save a lot of lives in the future.

**Meklit**

What do you say about the distribution of tobacco-related disease in Ethiopia? What do you do on reducing and preventing the distribution of the diseases at Addis Ababa University Medical school?

**Professor Frank**

I teach as many people as I can, students, friends, children, coworkers about the health dangers of smoking.....we all need to keep our children healthy and prevent a future epidemic of tobacco-related diseases

The "west" has seen this epidemic for decades.... African countries are in danger of the same smoking-related diseases, but education is the key.

**Meklit**

And finally, do you have anything you would like to say as a message to Ethiopian, African and to the world young students?

**Professor Frank**

I would advise all students to work hard and to see knowledge, above anything else, as their currency for personal success and for helping them to improve their society and make the world a healthier and happier place!

**Meklit**

Professor Frank I thank you on behalf of Nile newspaper for your time!

**Professor Frank**

Only, thank you for being so gracious and interviewing me, Meklit- it was a privilege.

# ቄንጠኛው (ልብወለድ) ክፍል 6

**ከባለፈው እትም የቀጠለ**

አረጋዊ ሰለሞን AS (3ኛ ዓመት የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ተማሪ)

Aregawisolo27@gmail.com

"…እኔ ነግሬ አለሁ! አዎ፡፡ እያንዳንድሽም የራሽን ሥራ! አለበለዚያ ሲቀላውጥ ያገኘሁት ተማሪ ካለ Automatically እፈርምበታለሁ፡፡ People, I am serious! ቀልድ አላውቅም፤ … እናንተ እዚያጋ ያላችሁ ደግሞ ኑ ወደዚህ፡፡ … Attendance ያልሞላችሁ ሙሉ…" መምህር ጌትነት ከግማሽ በላይ ተማሪዎች ተፈትነው እስኪ ወጡ ድረስ "አታድርግ! አታድርጊ…" የመሳሰሉ ትዕዛዛትን ደጋግመው ማዘዛቸውን አላቆሙም፡፡ ፈተና ላይ ንግግር ማብዛት የተፈታኙን ቀልብ እንደሚሰርቅ ጠፍቷቸው ይሆን?

ከፈተና የወጡ ተማሪዎች ከመማሪያ ክፍሉ ራቅ ብለው ገሚሶቹ ሃንዳውታቸውን ገልጠው ገሚሶቹም የተገለጠላቸው ሃንዳውት ላይ አፍጥጠዋል፡፡

አስመላሽንና ኤርሚያስን ጨምሮ አያና እና ቄንጠኛው "በዲጂታል ስቱዲዮ" አድርገው ወደ "ዶርም" እየሄዱ ነው፡፡

"ዛሬ በናትህ ኬድር ባይኖር ኖሮ ምን ይውጠኝ ነበር? ጭራሽ ሳልቸክል ገብቼ ጉድ…" አለ ቄንጠኛው ድንገት ንግግሩን ሳይቋል

"ሰርተሃል እንዴ አለው ኤርሚያስ፤ ሃሳቡን ሳይጨርሰው"

"ትቀልዳለህ ጀለሴ ጉዳዮ እኮ የግሬድ ነው፡፡ ባንዲራ ላለመስቀል የሚደረግ ጥረት፤ በዛ ላይ ሼባው መተረቻ እያደረገኝ፡፡ አስበሽዋል ግን ውጤት ከወረደ እንዴት "አዛ" እንደሚያደርገኝ?!"

"እንኳንም ዘንቦብሽ ድሮውም ጤዛ ነሽ አሉ፡፡ እውነታቸውን ነዋ እንኳን "ግሬዲሽ" ወርዶ ሁኔታሽም ከሼባው ጋር አልገጥምም ብሏል፡፡ አራምባና ቆቦ እኮ ነው የሆናችሁት፡፡ ሰኞ እና አርብ ነው እንዴ የተወለዳችሁት?" አለ አስመላሽ፡፡ ሰኞን እንደ መጥፎ አርብን ደግሞ እንደ ተወዳጅ ቀን በማድረግ የቄንጠኛውንና የመምህር ጌትነትን ሁኔታ ጋር እያመሳሰለ፡፡

"አትቀልድ እባክህ አንተ! እንዳንተ ከጠጃም የተወለድኩኝ መሰለህ እንዴ?" ቄንጠኛው የስላቁን ጥያቄ በጥያቄ መለሰ፡፡

"የውላችሁ እኔ ዛሬ ነፃ ነኝ እናንተም ነፃ ከሆናችሁ እንደ ልጅ መነታረኩን ተውትና ወጣ ብለን የሆነች ቦታ ደርሰን እንምጣ፡፡ በዚያ ላይ የማታው የባህል ማዕከል ልምምዳችን ወደ ማክሰኞ ተዘዋውሯል፡፡" አለ አያና የአንዳች ነገር ፍላጐት ያደረበት ይመስላል፡፡

እነቄንጠኛው ምን ጊዜም እንውጣ የሚል ሃሳብ ሲነሳ ፍቃደኞች መሆናቸውን አያና ተገንዝቧቸዋል፡፡ በመሆኑም ሃሳቡን እንደሚቀበሉት እርግጠኛ ነበር፤ በሃሳቡ ተስማሙ፡፡ አያናም ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም አንድ ነገር ማድረግ እንዳለበት አሰበ፡፡

እንደ ወትሮው ሁሉ ስለአንድ ጉዳይ ማውራታቸውን አሁንም ቀጥለውበታል፡፡

"ሰሞኑን ደግሞ የሴቶች ቀን ሊከበር ነው አሉ" አለ አስመላሽ፡፡

"የየትኞቹ ሴቶች?" አለና ቄንጠኛው አስመላሽን ጠየቀው፡፡

"የችኮቹ ነዋ! የኢትዮጵያ ችኮች በመሪ ቃል ምናምን ነው የሚከበር አሉ" አስመላሽ መለሰ፡፡ ኤርሚያስና አያና መልሱ ላይ ሳይሳተፉ ዝም ብለው ያዳምጣሉ፡፡

"ይሄኔ እኮ በጉባኤ ምናምን ይሆናል የሚያከብሩት፤ ቆይ የወንዶች የበዓል ቀን አለ እንዴ?" አለ ቄንጠኛው በምፀት፡፡

"ምን ነው መሰብሰብ አማረህ እንዴ?" አያና ለመጀመሪያ ጊዜ ጠየቀው፡፡

"እኔ?! ኧረ እኔ እንደዚህ ዓይነት ነገር አይመስጠኝም አስበሽዋል ግን አንተ እዛው ዱቅ ብለህ ሶስት አራት ገፅ "PR" ሲተርክልህ? ብትተኛ እኮ ቢያንስ ሁለት ህልም ታይበታለህ፤ ለዛም ፊልም የመሰለ ህልም ባይጠቅምህ እንኳን አይጐዳህም፤ ትዝናናለህ እረፍትም ታገኛለህ፡፡ እኔ በተፈጥሮ ጉባኤ ምናምን አይመስጠኝም፡፡" አለ ቄንጠኛው ዝቅ ያለ ሱሪውን ትንሽ ከፍ እያደረገ፡፡ ዶርም ገብተው ብዙ ካወሩ በኋላ "አዩ ምሳ ሰዓት ስለደረሰ አብረን ሄደን ከእኛ ጋር ትበላለህ ለዛሬ ከካፌ ጋር እናፋታህ" አለው ቄንጠኛው፡፡

"መልካም በዛው አድርገን የሆነ ቦታ ላይ እንሄዳለን፡፡" አለ አያና፡፡

ስድስት ኪሎ ተብላ በምትጠራው ቤት ውስጥ አራቱም ተሰባስበው ምሳቸውን ከበሉ በኋላ ልክ 10፡30 ሰዓት ሲል ከመናሃሪያው ዝቅ ብላ በምትገኘውና "በቦምብ ፍቅርሽ" ተብላ በምትጠራው ጠላ ቤት ውስጥ ገብተው ጠላቸውን መቸለስ ጀመሩ፡፡ አምስት ጆግ ጠላ ካጠናቀቁ በኋላ አያና ሂሳቡን ከፍሎላቸው ወደ ሌላኛው ቤት አመሩ ወደ ወንድማማቾች የባህል ምሽት፡፡

የባህል ምሽቱ ቤቱ ጣራው በከብቶች ቆዳ ተውቧል፡፡ ግድግዳው በባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ተሽቆጥቁጧል፡፡ አስተናጋጁን ጨምሮ በምሽት ቤቱ የሚሰሩ ሠራተኞች በባህል ልብስ ተውበው ይታያሉ፡፡ ምሽቱን ካሳመሩት የባህል ዘፋኞች መካከል አንዷ እነ ቄንጠኛው ከተቀመጡበት አካባቢ ሆና ግጥሟን ከዜማ ጋር በማቀናጀት እነ ቄንጠኛውን ታሞካሻለች፤ ትተችም አለች፡፡

ድንገት ወደ ቄንጠኛው ዞር አለችና ዘፈኗን ቀጠለች፡፡

"ቀበቶህ ተፈቶ

ሱሪህ ወርዷልና

ቀበቶህ ተፈቶ

ሱሪህ ወርዷልና

ጠበቅ አድርገህ እሰር

ሚስትህ እንዳትቀና

ከፍ አድርገህ እሰር

ሀበሻ ነህና፡፡

ምንም እንኳ ቄንጠኛው ትንሽ ሀፍረት ቢጤ ቢሰማውም ጨዋታው እጅግ ስለደራ ደስ ብሎታል፡፡ ከአያና በቀር ሌሎቹ እንደዚህ አይነት ቦታ ሄደው ስለማያውቁ አዲስ ነገር ሆኖባቸዋል፤ ምሽቱን ወደውታል፡፡

በአብዛኛዎቹ የባህል ምሽቶች ቤቶች የሚሸጡ መጠጦች ከሌሎቹ ጋር ሲነፃፀር ቀላል የማይባል የዋጋ ጭማሪ ስላላቸው ደጋግመው መጠጣት አልቻሉም፡፡ ቆይታቸው እየጨመረ በሄደ ቁጥር የእነቄንጠኛው ስሜት በደስታ እየተሞላ ሄደ፤ አዝማሪዋም ቅፅበታዊ ግጥሞችን በመፍጠር መዝፈኗን ቀጠለች፡፡

ማስታወሻነቱ ለነሰሎሞኖች (218) ይሁንልኝ፡፡

ይቀጥላል!!!

## ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን

የናይል ጋዜጣን ተነባቢነት ለማሳደግ የዝግጅት ክፍሉ የተለያዩ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡ እርስዎም አስተማሪ እና አዝናኝ የሆኑ

- የተለያዩ ጹሁፎች
- ማህበራዊ ሳይንሳዊ ኢኮኖሚያዊ እና ቴክኖሎጂ ነክ ጉዳዮች
- የካርቱን ስእሎች
- ቀልድ
- ግጥም

እና የመሳሰሉትን አዲሱ ጥበብ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር G5-02E በሚገኘው ቢሯችን ድረስ በመምጣት ወይም በኢሜል gracetsegi@gmail.com ይላኩልን፡፡

በናይል ጋዜጣ በቀጣይም ለእናንተ ይመጥናሉ ያልናቸውን የተለያዩ ጽሁፎች ማቅረብ እንደምንቀጥል እየገለጽን ለቀጣዩ ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ በአድራሻችን መላክ ወይም በኢሜል አታች ማድረግ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

ዝግጅት ክፍሉ

## ውድ የናይል ጋዜጣ አንባብያን

የናይል ሕዳር ወር እትም ላይ በዶ/ር አበባው ይርጋ ‹እኔ እንዲህ እላለሁ› በሚለው ፅሁፍ ላይ ለታየው መጠነኛ የአርትኦት ችግር እንዲሁም ‹የኤች አይ.ቪ ኤድስ ቀን ተከበረ› በሚለው ዜና ላይ በእግር ኳስ ጨዋታ የስነ- ምግባርና ፀረ-ሙስና ዳይሬክቶሬት ኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና መቆጣጠሪያ ዳይሬክቶሬትን 4 ለ3 ማሸነፉ እንዲታወቅልን እያልን ውድ አንባቢዎቻችንን ይቅርታ እንጠይቃለን፡፡

ዝግጅት ክፍሉ

# የራያ ቆቦ የባሕል የሙዚቃ ቡድን የራያ ቆቦን ባሕላዊ ሙዚቃዎች፣የአለባበስ ስርአት፣ ስነ-ቃሎችንና ባሕላዊ የግጭት አፈታት ስርአትን ለባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ አቀረበ










ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ